

በሕክምና ስህተት ዐሥር ዓመት የተኛው ኢትዮጵያዊ
ነብዩ ሲራክ

በገፅ 9



እድገቱ ለማነው? አስደናቂ እድገት ወይስ ተከታታይ ድህነት?
አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)

በገፅ 5



ጭቆናን ረሳን፤ ጭቆናን አነገስን!

በገፅ 4




# የቀለም ቀንድ

ቅጽ 3 ቁጥር 23 ታህሳስ 19 ቀን 2008ዓ.ም ዋጋው ብር 10.00


# በ"ፀረ ሰላም ኃይሎች" ማሳበብ እስከ መቼ? 2



## አቶ በቀለ ገርባ በድጋሚ ታሰሩ

• ሲፒጄ የኢትዮጵያ መንግሥት የኦሮሚያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጋዜጠኛ የሆነውን ፍቃዱ ምርካናን እንዲለቅ ጥሪ አቀረበ

የኦፌኮ ምክትል ሊቀመንበር አቶ በቀለ ገርባ ከኦሮሞ ተማሪዎች ተቃውሞ ጋር በተያያዘ ታሰሩ፡፡ አቶ በቀለ ገርባ ከዚህ በፊት ታስረው የ3 ዓመት ከ7 ወር በማረሚያ ቤት ቆይተው ባሳለፍነው 2007 ዓ.ም. መፈታታቸው ይታወቃል፡፡ አቶ በቀለ ማክሰኞ ታኅሣሥ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. በፖሊስ የተያዙ ሲሆን እስካሁን ፍርድ ቤት እንዳልቀረቡ የኦፌኮ ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ነጋ ገልጸዋል፡፡ አቶ በቀለ ነጋ የመድረክና የኦፌኮ የወጣቶች ሊግ ኃላፊ የነበሩት አቶ ደስታ ዲንቃም በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች መታራቸውን ተናግረዋል፡፡ በኦሮሚያ ክልል በርካታ ዜጎች አሁን እየታሰሩ እንደሆነ የሚገልጹት አቶ በቀለ ነጋ እስካሁን የታሰሩ ዜጎች ቁጥር ከ4000 በላይ ነው ብለዋል፡፡

በተያያዘ ዜና የዓለም የጋዜጠኞች ጥቃት ተከላካይ ኮሚቴ (ሲፒጄ) የኢትዮጵያ መንግሥት ከቀናት በፊት የታሰረውን የኦሮሚያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጋዜጠኛ ፍቃዱ ምርካና በአስቸኳይ እንዲለቅ መግለጫ አውጥቷል፡፡ የኦሮሚያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ለኦሮሞ ተማሪዎች ተቃውሞ ሰፊ ሽፋን መስጠቱን ተከትሎ ፈቃዱ ምርካና እንደታሰረ የገለጸው ሲፒጄ ጋዜጠኞች ከሁለቱም ወገን በተለይ ደግሞ የተጎጂዎችን ድምጽ መስማት ሙያው እንደሆነ ገልጿል፡፡ ታኅሣሥ 9 ቀን 2008 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ በመንግሥት የጸጥታና የደህንነት አካላት የተወሰደው ጋዜጠኛ ፍቃዱ ምርካና እስካሁን ያለበትም እንደማይታወቅ ሲፒጄ በዘገባው አስታውሷል፡፡

ታኅሣሥ 16 ቀን 2008 ዓ.ም. ሊካሄድ የነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ከመንግሥት ዕውቅና አልተሰጠውም

• <<የተገደሉ ሰዎችን አስከሬን ለመውሰድ የጸጥታ ኃይሎች እስከ አንድ ሺህ ብር ጠይቀዋል>>
ዶ/ር መረራ ጉዲና

ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተጠየቀበት

አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ነው

በገፅ 3

## ርእሰ አንቀፅ

# በ"ፀረ ሰላም ኃይሎች" ማሳበብ እስከ መቼ?

በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩት ሕገ መንግሥታትና ሌሎች ሕጎች ንጉሠ ነገሥቱንና ንጉሣዊ ሥርዓቱን የሚያገለግሉ ‹‹የመግዣ መሣሪያዎች›› እንደነበሩ ብዙ ይጻፋል፤ ይነገራል፡፡ የንጉሣዊ ሥርዓቱን በመቃወም የተጀመረው ‹‹ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት!›› የሚለው የአብዮት ዘመን መፈክር ሕዝቡ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት መሆን እንደሚገባውና ማንም ኃይል ከሕግ በላይ ሆኖ የሕዝቡን መብት እንዳይደፈጥጥ የሚያስገነዝብ እንደነበርም አይዘነጋም፡፡ ሁሉም በሕግ ፊት እኩል የሚሆንበትን ሥርዓት ለመፍጠር እንቅስቃሴ ከተጀመረ ከ40 ዓመታት በኋላም ግን የሕግ የበላይነት ጥያቄ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጉዳይ ወዘተ. አሁንም ወቅታዊና አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አሁንም ከረዥም ዘመናት በኋላ ከአገዛዝ መሣሪያነት የተላቀቁና ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት የሚያገለግሉ ጠንካራ ሥርዓታት (ኢንስቲትውሽንስ) መገንባት አልቻልንም፡፡

ጠንካራ ሥርዓታት የነገሡበትና ያበቡበት ኅብረተሰብን እውን ለማድረግ የሚቻለው የሕግ የበላይነትና በሕግ ፊት መንግሥትን ጨምሮ የሁሉም እኩልነት ሲረጋገጥ፣ እንዲሁም የሕግ አውጭው አካል የተሟላ ተቀባይነት/አመኔታ ሲኖረውና የፍትሕ አካላት በሙሉ ነጻነት ሲሠሩ ብቻ መሆኑን ምሁራን በሰፊው የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በሕዝብ ብዛቱና በመሬት ሥፋቱ ግዙፍ በሆነ፣ በአንድ ወጥነት ሳይሆን በልዩነትና በብዝሃነት ባሸበረቀ፣ ተፈጥሯዊውን ጨምሮ በርካታ የተቆላለፉ ችግሮች በተጋረጡበት አገር ደግሞ የሕግ የበላይነትና በሕግ ፊት የሁሉንም እኩልነት ለማረጋገጥ የሚቻለው የተሟላ የፖለቲካ ነጻነትን በማስፈን ብቻ ነው፡፡

የደርጉን ‹‹የቀላጤ አገዛዝ›› ትተን ባለፉት 25 ዓመታት ያለውን ሁኔታ በምናይበት ጊዜ፣ በአብዮቱ ዘመን ሲነሱ የነበሩት ዐበይት ጥያቄዎች አሁንም እንዳልተፈቱ እንገነዘባለን፡፡ አሁንም ከአራት ዐሥርት ዓመታት በኋላ ሕጎች የሚወጡት አገዛዙን ለማገልገል ነው፡፡ ሥርቆትና ቅሚያ (በዘመናዊ ስሙ ሙስና) ከመቼውም ጊዜ በላይ የገነነው ጠንካራ ሥርዓታት ባለመዘርጋታችን ነው፡፡ ኅብረተሰቡ ‹‹ከመክሰስ መከሰስ ይሻላል›› የሚለው የፍትሕ ሥርዓቱ ከፍተኛ ችግር ላይ የወደቀ በመሆኑ ነው፡፡ የመንግሥት አሠራርና እርምጃዎች ለኅብረተሰቡ ተገማች መሆን ያልቻሉትና ሕዝቡ የማይተማመንባቸው ጠንካራ ሥርዓታት ባለመገንባታችን ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በትራፊክ ችግር በዓለም ደረጃ ታዋቂነትን ማትረፍ የቻልነው ጠንካራ ሥርዓት ባለመገንባታችን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ዛሬ የወጣው ሕግ ነገ ይፈርሳል ወይም ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ አፍርሶ መገንባት፣ እንደገና ማፍረስ ዋና መገለጫችን ሆኗል፡፡ አሁንም አይጠየቄና ከሕግ በላይ የሆኑ አካላት አሉ፡፡ ጉዳዮች የሚፈጸሙት በጉቦ፣ በምልጃ፣ በብሔረሰባዊ ኔትዎርክ ነው ወዘተ፡፡

ሕገ መንግሥት የሚወጣው ኃይለኞችን በተለይም በሥልጣን ላይ ያሉት አካላት ሕዝቡን እንደፈለጉ እንዳያንገላቱ ልጓም ለማበጀት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በአምባገነናዊ አገዛዞች ውስጥ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ጨርሶ የለም፡፡ ሕግ የሚወጣው አገዛዙን ለመጠበቅና ተቀናቃኞችን ወይም የመብት ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎችን ለመቅጫና ለመጨፍለቂያነት ነው፡፡ ለዚህ ነው ከዴሞክራት መሪዎች ይልቅ አምባገነኖች ስለሕግና ሕገ መንግሥት መከበር በሰፊው የሚያወሩት፡፡ አምባገነኖች ሕጉ በእነሱ ላይ ልጓም የሚያበጅ ሳይሆን ጠባቂያቸው በመሆኑ ‹‹ሕግ ይከበር፤ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለማስከበር በቁርጠኝነት እንሠራለን ወዘተ.›› እያሉ አበክረው ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ በዘመነ ኢሕአዴግ እንደዚህ ያለውን ዲስኩር እስኪሰለቸን ድረስ ሰምተነዋል፡፡ በቅርቡም ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በጎንደርና በኦሮሚያ የተቀሰቀሱትንና የብዙ ዜጎች ሕይወት የጠፋባቸውን ግጭቶች አስመልክተው ከአቶ መለስ በኮረጁት የንግግር ቅላጼ ሲዝቱና ስለሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ መጠበቅ ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡ ፀረ ሰላም ያሏቸው አካላት ‹‹ተመጣጣኝ›› ቅጣት እንደሚያገኙም ተናግረዋል፡፡ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በመጠበቅ ስም መብታቸውን የሚጠይቁ ዜጎችን በመግደል፣ በጅምላ በማሰርና በማሰቃየት ችገሮችን ለመፍታት ሲሞከር ታዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ ደግሞ ጥያቄዎች መልካቸውን ቀይረው ሰላምና ጽጥታ የሰፈነ ቢመስልም ግፉና መከራው ይበልጥ ቁጭትንና ለበቀል መነሳሳትን ማርገዙ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ የዓለም ታሪክ የሚያስተምረን በመከራ ውስጥ ያለፉት አካላት የለየላቸው በቀለኞችና ነብሰ ገዳዮች መሆናቸውን ነው፡፡ በሩዋንዳና በቡሩንዲ የሆነውን ዘግናኝ ሁኔታ፣ በጎረቤታችን በደቡብ ሱዳን የሚሆነውን ሁሉ ማየት ይቻላል፡፡

ኔልሰን ማንዴላ እንዳሉት የትግሉን ሁኔታና አቅጣጫ የሚወስነው ተጨቋኙ ሳይሆን ጨቋኙ ራሱ ነው፡፡ በአገራችን አሁን የተያዘው መንገድ በጣም አደገኛ ነው፡፡ ከአገሪቱ ሀብት ተጠቃሚ የሚሆኑት በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ በሀብታሙና በድሃው መካከል ያለው ልዩነት የትየለሌ ነው፡፡ በመንግሥት ሌቦች የሚካሄደውን ጨምሮ በሚያስፈራ ደረጃ ሌብነት ዋና መገለጫችን እየሆነ ነው፡፡ የሕግ የበላይነት ደብዛው የለም፡፡ የፖለቲካ ነጻነቱ በጣም አሳዛኝ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የሃይማኖትና የብሔረሰብ አክራሪነት እየጨመረ ነው ወዘተ፡፡ እነኝህ አንገብጋቢ ችግሮች መልስ ይፈልጋሉ፤ መልስ ካለተሰጣቸው ግን ሌላ ቅርጽ መያዛቸው የሚቀር አይሆንም፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩ ወደራስ ወደውስጥ ከማየትና ሁኔታዎችን በሰከነ ሁኔታና በጥንቃቄ ገምግሞ መፍትሔ ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ሁልጊዜም በ‹‹ፀረ ሰላም ኃይሎች›› እያሳበቡ መኖር አይቻልም፡፡ በጽኑ መሠረት ላይ የተገነባ ሥርዓት አለን የሚለውን ተረት ተረት ወደጎን ብሎ ወሳኝ በሆኑና መፍትሔ በሚያስፈልጋቸው ብሔራዊ አጀንዳዎች ላይ አርቆ አስተዋይነት የተሞላበት ውሳኔ ማሳለፍ፤ ከሚመለከታቸው ኃይሎች ጋር መምከር እና የዜጎችን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ መሣሪያና የገንዘብ ክምችት ለጊዜው ደረትን የሚያስነፋና የሚያስፎክር ቢመስልም ከውድቀትና ከውርደት እንደማያድን የነፕሬዚዳንት ጋዳፊ መጨረሻ በሚገባ ያስተማረን ይመስለናል፡፡

## ትዝብት

ሩት አማኑኤል

# ችግር ቀፍቃፊ ዩኒቨርሲቲዎቻችን

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአገርና ለዓለም የሚተርፉ የጥናትና ምርምር ውጤቶች የሚፈልቁባቸውና ዕውቀት የሚመነጭባቸው ብርቅዬ አምባዎች ናቸው፡፡ አገራችን ዩኒቨርሲቲዎች በአንጻሩ ከአካዳሚ ዕውቀት ይልቅ የአገዛዝ ርዕዮተዓለም የሚጠናባቸው፤ ከኅብረት ይልቅ ልዩነትና ክፍፍል የሚቀፈቀፍባቸው ማዕከላት ሆነዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቻችን የብሔረሰብ እና የሃይማኖት ወኪል ነን የሚሉ ቡድኖች የሚተራመሱባቸው ማዕከላት ከሆኑ ሰነባብተዋል፡፡ በየዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በብሔረሰብ ተከፋፍለው ‹‹የራሴ›› የሚሉትን ባህል (የአለባበስና የጭፈራ ዓይነት ወዘተ.) ለማሳየት በእኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ወድድር ተጠምደዋል ለማለት ይቻላል፡፡ ውድድሩ ብዙውን ጊዜ ወደ ግጭት ሲተላለፍም ታዝበናል፡፡ ሃይማኖትም ራሱን የቻለ የውድድርና የልዩነት መነሻ እየሆነ ነው፡፡ ተማሪዎች ባህልን በማስተዋወቅ ስም የብሔረሰብ እና የሃይማኖት ልዩነትን መሠረት አድርገው መንቀሳቀሳቸው የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችን ቡራኬ እንደሚያጎናጽፋቸውና ትምህርታቸውን ‹‹አጠናቅቀው›› ወደአገር ቤት ሲመለሱ ሹመት እንደሚያስገኝላቸው ይገነዘባሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲ የብሔረሰብና የሃይማኖት ውድድር ሳይሆን አካዳሚያዊ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት አምባ መሆኑን የሚያምኑት ተማሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ በመምጣት ላይ ነው፡፡

ከሁሉ አስቀድሞ፣ ዩኒቨርሲቲዎች የተለያዩ ብሔረሰቦች ባህሎች የሚተዋወቁባቸው ምክር ቤቶች እንደሆኑ አድርገው የሚያስቡ ወገኖች ከፍተኛ ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ይኸውም ከላይ እንደተጠቀሰው ዩኒቨርሲቲ የዕውቀት አምባ ሆኖ ሳለ እነኝህ ወገኖች የዩኒቨርሲቲዎችን ዋና ተልዕኮ ወደ ጎን ገሸሽ በማድረግ የባህል ማዕከል እንዲሆኑ ይፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ ባህል አይተዋወቅ የሚል አቋም ሊኖር አይችልም፡፡ ችግሩ፤ በአንድ በኩል ተማሪዎቻችን ባህል ለማስተዋወቅ የተለያዩ የጭፈራና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን ሲያዘጋጁ ለዋናው ዓላማቸው (ንባብ፣ ምርምር ወዘተ.) በቂ ጊዜ አይሰጡም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእኔ ባህል ከአንተ ይበልጣል የሚል አላስፈላጊና አጥፊ ውድድር ይፈጥርና ግጭት ይጋብዛል፡፡ በዚህ ምክንያት ብዙ ግጭቶች መከሰታቸውም እውነት ነው፡፡

የወቅቱ የዩኒቨርሲቲያችን ሁኔታ በጣም አስቸጋሪና አሳሳቢ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የውይይትና የክርክር ክበቦችን አቋቁሞ የተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን እያነሱ በእርስ በርስ ውይይትና ክርክር ዕውቀትን ከማበልጸግ ይልቅ በጠባብ ብሔረሰባዊ ማንነትና በድርጅት ፍርፋሪ ለቃሚነት መለከፍን ከመበስበስ ሌላ ምን ይሉታል?

በዲኦንሔር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃላ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ

**ሥራ አስኪያጅ**
አበበ ውቤ

**ዋና አዘጋጅ**
ሙሉቀን ተስፋው
0910159783
mulukentesfaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297


**ሪፖርተር**
ትሑት ጥላሁን

**አምደኞች**
መስከረም አበራ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)
አክሎክ ቢራራ (ዶ/ር)
ሩት አማኑኤል
መብራቱ በላቸው
በሪሁን አዳነ
ታዲዮስ ታንቱ
ነብዩ ሲራክ (ከሳውዲ አረቢያ)

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡ 0910159783
0919396240

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ስልክ፤ 0911 18 09 33

**አታሚ**
<<ሶፍ ሚክ ማታሚያ ቤት
ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 04
የቤት ቁጥር 64



## ዜናዎች

# ታኅሣሥ 16 ቀን 2008 ዓ.ም. ሊካሄድ የነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ከመንግሥት ዕውቅና አልተሰጠውም

### •‹‹የተገደሉ ሰዎችን አስከሬን ለመውሰድ የጸጥታ ኃይሎች እስከ አንድ ሺህ ብር ጠይቀዋል›› ዶ/ር መረራ ጉዲና

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ሕገ መንግሥታዊ ጥሰቶችን በሚቃወሙ ሕጋዊና ሰላማዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን በኃይል እርምጃ ለማስቆም እየተፈጸሙ ያሉት ግድያዎችና አፈናዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ እንዲሁም በወንጀሉ ተዋናይ የሆኑት የመንግሥት ታጣቂዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ጠየቀ:: መድረክ ታኅሣሥ 13 ቀን 2008 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላንን በመቃወም በወጡ ወጣቶች እና በጎንደር ነዋሪዎች ላይ የተፈጸሙት ጭፍጨፋዎች መድረክን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳስበውና ድርጊቱን በጽኑ እንደሚያወግዘው ገልጿል:: በመተማ አካባቢ የትግራይ ተወላጆች ሀብት ንብረታቸው ወድሞ ከቀያቸው መባረራቸውም መድረክን ያሳስበዋል ሲል በመግለጫው ጠቅሷል:: መድረክ እንደገለጸው በኦሮሚያ ክልል መንግሥት ግድያው አባብሶት እጅግ አሳዛኝ የመብት ጥሰቶች ተከስተዋል:: በምዕራብ ወለጋ ዞን ጫንቃ ላይ ወይዘሮ አልማዝ የተባሉ እማውራና ልጃቸው በጥይት ተደብድበው ከሞቱ በኂላ ቀብራቸው ተከልክሎ ለሦስት ቀናት እንዲዘገይ መደረጉና በሌሎች አካባቢዎችም በመንግሥት የጸጥታ አካላት የተገደሉ ሰዎች አስከሬን ቀብር መከልከሉን መግለጫው ይፋ አድርጓል::

ዶ/ር መረራ ጉዲና ቀብር የተከለከሉ ሰዎችን አስመልክቶ ከጋዜጠኞች ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ወደ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ወሊሶ አካባቢ በመንግሥት የጸጥታ አካላት የተገደሉ ዘመዶቻቸውን ለመቅበር አስከሬን ሲጠይቁ እስከ አንድ ሽህ ብር እየተጠየቁና አሸባሪ ናቸው ብለው ፈርመው እንዲወስዱ እየተደረገ ነው›› ሲሉ ተናገረዋል:: ዶ/ር መረራ ይህን ድርጊት የደርግ መንግሥት በቀይ ሽብር ገድሎ ተመሳሳይ ነገር ይፈጽም እንደነበር አስታውሰው የኢሕአዴግ መንግሥት በዜጎች ላይ እየሰደ ካለውን ሰብአዊነት ከጎደለው እርምጃ እንዲቆጠብ አሳስበዋል::

> ዶ/ር መረራ ይህን ድርጊት የደርግ መንግሥት በቀይ ሽብር ገድሎ ተመሳሳይ ነገር ይፈጽም እንደነበር አስታውሰው የኢሕአዴግ መንግሥት በዜጎች ላይ እየሰደ ካለውን ሰብአዊነት ከጎደለው እርምጃ እንዲቆጠብ አሳስበዋል

መድረክ በረኀብ ለተጎዱ ወገኖች የሚቀርበውን የእርዳታ እህል አሰጣጥን በተመለከተም መንግሥትን ወቅሷል:: በረኀብ ለተጎዱ ወገኖቻቻችን ከዓለም ዓቀፍ ለጋሾች የተገኘው የእርዳታ እህል ሥርጭት እጅግ በሚያሳዝን መልኩ በሙሰኛ የወረዳና የቀበሌ አስተዳዳሪዎች እጅ በመግባቱ ተጎጅው ሕዝብ ለባሰ ችግር እንደተጋለጠ የሚያትተው መግለጫው፤ በረኀብ የተጎዱ ወገኖች የኢሕአዴግ አባልና የተቃዋሚ ድርጅቶች አባልና ደጋፊ አለመሆናቸው እንዲረጋገጥ እየተደረገ የሚሰጠው እርዳታ ከሰብአዊነት ተግባር ውጭ መሆኑን በመግለጽ በጽኑ ኮንኗል::

በተያያዘ ዜና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ፣ ሰማያዊ ፓርቲና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ፓርቲዎች በጋራ ታኅሣሥ 17 ቀን 2008 ዓ.ም. ሊያደርጉት የነበረው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰለፍ በመንግሥት መከልከሉ ተነግሯል:: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት ለመደረክ በላከው ደብዳቤ የተጠየቀው ቦታ በልማት ምክንያት የትራፊክ መጨናነቅ፣ ትላልቅ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያሉበት ከመሆኑም በላይ አሁን ባለው የወቅቱ ሁኔታ አንጻር ዕውቅና ለመስጠት እንቸገራለን ሲል መልስ መስጠቱ ታውቋል::

# ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተጠየቀበት



### በተመሳሳይ ከጌታቸው ሽፈራው ጋር አምስት የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል

ታኅሣሥ 15 ቀን 2008 ዓ.ም. ጠዋት 2፡00 ሰዓት ከቤቱ ወደ ሥራ ቦታ ሲሄድ ሲቪል በለበሱ የደህንነትና የፌደራል ፖሊስ አባላት መያዙ ተገለጿል:: ጋዜጠኛ ጌታቸው ቤቱ ተፈትሾ በማዕከላዊ የታሰረ ሲሆን ቅዳሜ ታኅሣሥ 16 ቀን 2008 ዓ.ም. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ቀርቦ የፌደራል ፖሊስ መርማሪ የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆበታል:: ጌታቸው ሽፈራው የተከሰሰበት በሽብር ወንጀል ተጠርጥሮ ሲሆን ማንም ጠያቂ እየጎበኘው እንዳልሆነ የሥራ ባልደረባው በላይ ማናየ ለቀለም ቀንድ ጋዜጣ ተናግሯል::

ጌታቸው ሽፈራው የሰማያዊ ፓርቲ ልሳን በሆነችው የነገረ ኢትዮጵያ ዋና አዘጋጅ ሲሆን ቀደም ሲል በመሰናዘሪያ ጋዜጣና በላይፍ መጽሔት በጸሐፊነት ይሠራ እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ጌታቸው ሽፈራው ወደ ጋዜጠኛነት ሙያ ከመምጣቱ በፊት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ባለው የፖለቲካ አቋም ከሥራ መባረሩን በላይ ማናዬ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጿል::

በተመሳሳይ ከጌታቸው ሽፈራው ጋር አምስት የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በቁጥጥር ሥር ውለዋል:: ታኅሣሥ 15 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥጥር ሥር የዋሉት ቴዎድሮስ አስፋው፣ ዳንኤል ተስፋዬ፣ ፍሬው ተክሌ፣ ኤርሚያስ ጸጋዬና ሸዋታጠቅ ኃይለመስቀል ናቸው:: ሸዋታጠቅ ኃይለመስቀልና ዳንኤል ተስፋዬ ከአቶ ጌታቸው ሽፈራው ጋር ፍርድ ቤት ቀርበው የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ተሰጥቷቸዋል:: በዚህም መሠረት ጥር 14 ቀን 2008 ዓ.ም. ድጋሚ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ይሆናል::

# “የፖለቲካ መጻሕፍት እንዳንሸጥ ፖሊስ እየከለከለን ነው” መጻሕፍት አዟሪዎች

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ መጻሕፍት አዟሪዎች የፖለቲካ መጻሕፍት እንዳይሸጡ በፖሊስ ቁጥጥር እየተደረገባቸው መሆኑን ገለጹ:: መጻሕፍት አዟሪዎች እንደገለጹት ክልከላ ከሚደረግባቸው መጻሕፍት መካከል ዶ/ር መረራ ጉዲና በቅርቡ ያሳተሙት መጽሐፍ፣ ‹‹በምርኮ የተያዘ ሕዝብ›› የሚለው በበሪሁን አዳነ የተሰናኘ መጽሐፍ እና የፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ‹‹አዳፍኔ›› ይገኙባቸዋል:: ከሳምንት በፊት ከላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ሲያዞሩ የተገኙ 5 ጓደኞቻቸው በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የጠቀሱት አዟሪዎች ቁጥጥሩ ቢኖርም አሁንም መጻሕፍቱን በመሸጥ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል::

# ሰመጉ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ጠየቀ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ታኅሣሥ 11 ቀን 2008 ዓ.ም. ባወጣው መግለጫ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ልዩ ዞን የጋራ ማስተር ፕላን ተቃውሞ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ጠይቋል:: ከኀዳር 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተሞችን የተቀናጀ የማስተር ፕላን በመቃወም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በአዲስ አበባ ዙሪያ ልዩ ዞን ከተሞች፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌና በምሥራቅ ሐረርጌ እንዲሁም በሌሎች የኦሮሚያ ዞኖች በሚገኙ በርካታ ከተሞች በተለያዩ የኅብረሰብ ክፍሎች በሚያካሂዱት የተቃውሞ ሰልፍ ላይ የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በወሰዱት እርምጃ በርካታ ዜጎች መገደላቸውን፣ ብዙዎችም መታሰራቸውን እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት መውደሙን በጋዜጣዊ መግለጫው ሰመጉ አትቷል::

ሰመጉ እንደገለጸው ረቂቅ ማስተር ፕላኑ ለሕዝብና ለባለሙያዎች ቀርቦ ግልጽ ውይይት ሊደረግበትና ሊተች ሲገባው ለዓመታት በሚስጥር መያዙ ለጥርጣሬ፣ ለውዥንብርና ደም ላፋሰሰ ተቃውሞ መንስኤ ሆኗል:: በተጨማሪም ዜጎች በሰለማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን ሊገልጹበት የሚችሉበት መንገድ አለመመቻቸቱ ችግሩን የበለጠ አባብሶታል:: የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች የተጠቀሙት ኃይል ተመጣጣኝ አልነበረም የሚለው የሰመጉ መግለጫ ይህም ከመነሻው ሰላማዊ የነበረውን የዜጎች ተቃውሞ ግብታዊ መልክ እንዲይዝና ለዜጎች ሞት፣ አካል ጉዳት፣ ለሕዝብና ለግል ንብረት ውድመት መንስኤ እንዲሆን አድርጎታል:: ሰመጉ በዜጎች ላይ የተፈጸሙ ሰብአዊ ጥፋቶችን በመመርመር ላይ መሆኑን ገልጾ ይህን ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት ያስፈለገበት ምክንያትም እስካሁን ከደረሰው በላይ የከፋ ጉዳትና የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዳይደርስ ሁሉንም ወገን ለማሰሳብ ነው ብሏል::

# አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ነው

መንግሥት በድርቅ ሳቢያ ለርሃብ የተጋለጡ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከአስር ሚሊዮን በላይ እንደሆነ በመጥቀስ በይፋ የእርዳታ ጥሪ ያቀረበ ሲሆን የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የተረጂዎች ጠቅላላ ቁጥር ወደ 18 ሚሊየን ማሻቀቡን ገልጸዋል:: የድርቁ አደጋ ከባድ መሆኑን በመግለጽ ለቀረበው የእርዳታ ጥሪ ፈጣን ምላሽ እንደሚያስፈልግ የተናገሩት የእንግሊዝ የውጭ ተራድኦ ሚኒስቴር በምግብ ዋስትና ኘሮግራም ድጋፍ የሚያገኙት 7.9 ሚሊየን ሰዎችን ጨምሮ የተረጂ ዜጎች ቁጥር ወደ 18 ሚሊየን መጠጋቱን ገልጸዋል::

በተያያዘ ዜና የተቃዋሚ ፓርቲዎች የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች የኢህአዴግ አባልነትና የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ አለመሆናቸው እየተጠየቁ ነው የሚሰጣቸው ብለዋል:: መድረክ ባለፈው ሳምንት በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲህ አይነቱ አሰራር ሰብዓዊነት የጎደለው እንደሆነ ጠቅሶ ለተጎጅዎች የሚቀርበው የምግብ እህልም በሙሰኛ የወረዳና የቀበሌ አስተዳዳሪዎች እንደሚመዘበር አስታውቋል::

## ወቅታዊ

# ጭቆናን ረሳን፤ ጭቆናን አነገስን!

በወንበዴነት፣ በሽፍትነትና በዐረብ ቅጥረኛነት ሲከሰስ የነበረው ሕወሓት/ኢሕአዴግ ተቀናቃኞቹን በፀረ ሰላምነት፣ በሽፍትነትና በሻዕቢያ ተላላኪነት ሲከስ ከማየት የበለጠ የአገራችንን የአፈና ፖለቲካ ቀጣይነት የሚያረጋግጥ አብነት የለም። እስከምናውቀው ድረስ ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር እንደ አብዛኞቹ የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ብዙሃኑ ሕዝብ በእልልታና በሆታ አልተቀበለውም። በእርግጥ እልል እያሉ፣ ከበሮ እየመቱና ፈንድሻ እየበተኑ በታላቅ ደስታና የአሸናፊነት ስሜት የተቀበሉት ወገኖች ነበሩ። ይሁን እንጂ በኢሕአዴግ መምጣት የተከፉና የተናደዱ ብዙ ወገኖች እንደነበሩም የታወቀ ነው። የሆነ ሆኖ፣ የኢሕአዴግ መሪዎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚገነቡ፣ የሕዝቡን በነጻነት የመደራጀትና ሐሳቡን የመግለጽ ወዘተ. መብቱን እንደሚያከብሩ አበክረው በመግለጻቸው ብዙ ሰዎች ከፍተኛ ተስፋ ነበራቸው። ቃል በተገባው መሠረት መጀመሪያ በሽግግር መንግሥቱ ቻርተር ቀጥሎም በሕገ መንግሥቱ እነኝህንና ሌሎችን መብቶች የሚመለከቱ ሕጎች ተደነገጉ። ብዙዎች ደስ አላቸው። ‹‹ጭቆናን ለማስወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት ታግለዋል፤ በትግሉ ብዙዎች ተሰውተዋል፤ ቁርጠኛ ናቸው፤ እንደግፋቸው›› ያሉ ወገኖች በስደት ከሚኖሩባቸው አገራት ተመልሰው በፖለቲካው ሒደት መሳተፍ ጀመሩ።

የሚያሳዝነው የተገባው ቃል ሁሉ በተግባር መታየት ባለመቻሉ ብዙዎች ተስፋ ያደረጉትን ማግኘት አልቻሉም። በዚህ ምክንያት ብዙዎች ድርጅቱን ተሰናብተው ወደየመጡበት ለመመለስ ተገድደዋል። ብዙዎች እንደሚሉት አሁንም ከአምባገነንዊ አገዛዝ አልወጣንም። የቅርጽ ካልሆነ በስተቀር አሁንም እዚያው ከነበርንበት ላይ ነን። በዚህ እጅግ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ለመገኘታችን ደግሞ (የመጠን ልዩነት ካልሆነ በስተቀር) ሕዝቡም አገዛዙም ተጠያቂነት አለባቸው።

በአገራችን፣ የቀበሌ ሹመኞች ያለማንም ጠያቂ ኅብረተሰቡን የሚያሸብሩበት ጊዜ ነበር። ሰዎች (በእስር ላይ ያሉት ጭምር) ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ በአደባባይ የሚረሸኑበት ጊዜ ነበር። ወጣቶች ያለ ፍላጎታቸው በሹመኞች እየተሳደዱ የሚታነቁበትና ወደ ብሔራዊ ውትድርና የሚጋዙበት ጊዜ ነበር። አርሶ አደሮች የለፉበትን ሰብል ያለፍላጎታቸው በወደቀ ዋጋ እንዲሸጡ የሚደረግበትና ኮታ እንዲከፍሉ የሚገደዱበት ጊዜም ነበር። በደርግ ዘመን እነኝህና ሌሎች አስከፊ ጭቆናዎች ነበሩ።

ከደርግ አገዛዝ ውድቀት በኋላ፣ ‹‹ሕዝቡ የጭቆናን አስከፊነት ከበቂ በላይ ስላየ፣ መብቱን አሳልፎ አይሰጥም፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ይታገላል፣ በነጻነት ስለመደራጀትና ስለመጻፍ ወዘተ. መብቶቹ ዘብ ይቆማል፤ መሪዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት እንዲዘረጋና የጭቆና ሥርዓት እንዳያንሰራራ ይዋደቃል›› ወዘተ. ይባል ነበር። የሆነው ግን ያ አይደለም። አብዛኛው ሕዝብ አሁንም እንደ ትናንቱ ጭቆናውን በፀጋ ተቀብሎታል። ‹‹ሕዝቡ ጭቆናንና የጭቆናን አስከፊነት አይተነዋል፤ ጭቆና ሰውን ከሰው በታች የሚያደርግ አስከፊ ነገር ነውና ዳግመኛ ልንሸከመው አንችልም፤ አንፈቅድም›› ማለት አልቻለም። በተለያየ ምክንያት ተከፋፍሏል።

ካሉት ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎችና ከአገሪቱ ታሪክ አኳያ በአገራችን ሊኖር የሚገባውን የዴሞክራሲ እድገት ደረጃ ከማየት ይልቅ ‹‹ኢሕአዴግ ከደርግ ይሻላል›› ብለው ሥርዓቱን የሚደግፉ ወይም የማይቃወሙ ወገኖች አሉ። እነዚህ ወገኖች ጭቆና መኖሩን ባይክዱም ‹‹ጭቆናው ከደርግ ያነሰ ነውና እንታገስ፤ በሒደት መሻሻሎች ይኖራሉ›› የሚሉ ናቸው። በሙሉ ልብ ‹‹ዴሞክራሲ በአንድ ጀንበር አይገነባም፤ ሒደት ነው፣ አሜሪካኖች ዴሞክራሲን ለመገንባት 200 ዓመታት ፈጅቶባቸዋል›› ወዘተ. የሚሉም አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጭቆና መኖሩን ቢቀበሉም መብታቸውን ለማስከበር ራሳቸው የማይሳተፉ ነገር ግን ሁሉንም ሥራ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲሠሩላቸው የሚፈልጉ ወገኖችም አሉ። እነኝህ ኃይሎች፣ ራሳቸው የፖለቲካ ተሳትፎ አያደርጉም፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በገንዘብም ይሁን በሌላ መንገድ አይደግፉም፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለውጥ ባለማምጣታቸው ግን ይበሳጫሉ፤ ሁልጊዜም ተቃዋሚዎች እንደማይረቡና ተስፋ እንደማይጣልባቸው ከመግለጽ አይቦዝኑም። መነሻቸው የተለየ ቢሆንም ልክ እንደ ኢሕአዴግ ‹‹ምን ፓርቲ አለ!?›› የሚሉ ናቸው።



ሌሎች ደግሞ አሉ። በሚያሳፍርና በሚያስፈራ ሁኔታ የደርግን ሥርዓት የሚናፍቁና የሚያደንቁ ኃይሎች በአገራችን በርከት ያለ ቁጥር አላቸው። እነዚህ ወገኖች ያላቸው የፖለቲካ ተሳትፎ በጣም ከባድ ነው። የተሳትፏቸው መነሻ ግን ኢሕአዴግን ከመጥላት እንጂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ከማፍቀር የመጣ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ከየት ያወቁትን? አንዳንዶች ‹‹በሥልጣን ላይ በነበርንበት ጊዜ ያጠፋነው ጥፋት የለም›› እያሉ ሲጽፉ እየታዘብን ነው። ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት የዴሞክራሲ ትግሉ በጎ መልክ እንዳይኖረው ያደረጉት ኃይሎች እነዚህ ናቸው ማለት ይቻላል። በአገር ውስጥም ይሁን በውጪ አገራት በሚንቀሳቀሱት ተቃዋሚ ኃይሎች ውስጥ እየገቡ የሚያምሱት እነዚህ ወገኖች ናቸው። አሁንም በከተማችን ‹‹የመንጌ›› አድናቂዎችና ናፋቂዎች እስካሉ ድረስ ዴሞክራሲ የከተማው ብቸኛ ወሬ መሆን አልቻለም ማለት ነው። ርዕያችን ወደፊት ወደ ብሩኅ ተስፋ ሳይሆን ወደኋላ ወደ ወደቀውና መውደቅም ወደነበረበት አገዛዝ እስከሆነ እና አብዛኛው ሕዝብ ሥልጣን ሊያዝ የሚገባው በነጻና ፍትሐዊ ምርጫ (በዴሞክራሲ) ብቻ መሆን አለበት ብሎ እስካላመነ ድረስ አደጋ አለ።

ከኢሕአዴግ መምጣትና በሥልጣን ላይ መቆየት በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀሙ ኃይሎች ደግሞ አሉ። እነኝህ፣ ኢሕአዴግ ምን ያህል ይበልጥ ጨቋኝ እየሆነ ቢሄድም ድጋፋቸውን የማያቋርጡ ወገኖች ናቸው። ከድርጅቱ ተጠግተው መሬት ሸጠው የከበሩ፣ በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ በሚገርም ፍጥነት ሚሊየነር የሆኑ፣ በየክልሉ በብሔረሰብ መብት ስም እየነገዱ ሥልጣን የያዙ ወዘተ. ዜጎች ‹‹የደህንነታችን መሠረት ኢሕአዴግ ነው፤ እስከመጨረሻው እንደግፈዋለን›› ቢሉ ሊገርም አይችልም። ጭቆናን ከመቀበል አልፈው ሌሎች እንዳይታገሉ መሰናክል የሚፈጥሩ ናቸው።

በደርግ የመጨረሻዎቹ ዓመታትና ከዚያ ወዲህ የተወለደውና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣትም አለ። ይህ ኃይል ከቁጥሩ መብዛት በተጨማሪ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለው ጉጉት ከፍተኛ ቢሆንም አገዛዙና የተወሰኑ አክራሪ ወገኖች የሚያራግቡት ጠባብ የብሔረሰብ ተኮር ፖለቲካ ሰለባ በመሆኑ በጋራ መታገል አልቻለም። ሌሎች በፈጠሩት ቅርቃር ውስጥ የገባ አሳዛኝ ትውልድ ነው ማለት ይቻላል።

የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን እንደሚነግሩን እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱን ኃላፊነት ካልተወጣ፣ የሚገባውን ካልጠየቀ በስተቀር ምን ያህል ውብ ሕገ መንግሥት ቢኖር ፍሬ የለውም። ምሁራኑ እንደሚገልጹት ስለዴሞክራሲና ስለ ሰብአዊ መብት ጥበቃ የሚስገነዝቡ አንቀጾችማ የስታሊኗ ሶቪየት ኅብረት ሕገ መንግሥትም በብዛት ነበሩት። ቁም ነገሩ፣ ሕገ መንግሥት በተቀዳሚነት የመንግሥትን ኃይል ለመወሰንና ዜጎችን ለመጠበቅ የሚወጣ ሰነድ መሆኑን አምኖ ለተፈጻሚነቱ የሚታገል ሕዝብ ያስፈልጋል። ያ ካልሆነ እንደምናየው ስለሕገ መንግሥቱ የሚጨነቀውና በሕገ መንግሥቱ የሚጠቀመው ገዥው ኃይል ይሆናል።

ኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች በተለይ ሕወሓትና ብአዴን የምሥረታ በዓላቸውን በሚያከብሩበት ጊዜ ሁሉ ክላሽንኮቭ ያነገቱ፣ ቁምጣ ሱሪ የታጠቁና ሽበጥ ጫማ ያደረጉ ታጋዮችን በቴሌቪዥን መስኮት መመልከት የተለመደ ነው። እነዚህ ወገኖች የታገሉት ጭቆናን ለማስወገድና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ስለመሆኑ ብዙ ተብሏል፤ ብዙ ተነግሯል። እስካሁን እንደታየው አገዛዙ የሚሄድበት መንገድ ግን ጭራሽ ከዚህ አስተሳሰብ ጋር የተጣላ ነው። ለማኅበራዊ ፍትሕ ሲሉ እንደታገሉ የሚነግሩን ሰዎች ዛሬ ከበርቴዎችና ቢጠሯቸው የማይሰሙ ባለሀብቶች መሆናቸውን ሁሉም ያውቀዋል። በአብዮት ዘመን የአፄ ኃይለሥላሴ ባለሥልጣናት ‹‹ሕዝቡን ጭሰኛ አደረጉት›› ተብሎ ብዙ አመጽ ነበር። እውነትም ትልቅ ጭቆና ነበር። መሠረታዊው ነጥብ ‹‹ይህን ችግር በዘመነ ኢሕአዴግ ተሻግረነዋል ወይ?›› የሚለው ነው። ከወረዳ እስከ ፌደራል ድረስ ያሉ ሹመኞች በየቦታውና በተለያየ ሰው ስም መሬት የላቸውም ወይ? ቤት አልገነቡም ወይ? ትልልቅ የንግድ ኢምፓየሮችን አልተገነቡም ወይ?

የኢሕአዴግ መሪዎች ከበርቴነት እጅግ ዘመናዊና ውስብስብ ይዘት ያለው ነው። በአንድ በኩል ከመሬት ጋር የተያያዘ ካፒታል አፍርተዋል። የዚህ ጉዳይ እውነትነት አልፎ አልፎ በሚታሠሩት ባለሥልጣናት ይፋ ሆኗል። አቶ መለስ ዜናዊም በአንድ ወቅት መንግሥታቸው ሙስናን የሚታገለው አንድ እጁን ተይዞ እንደሆነና የመንግሥት ሌቦች ያሏቸው አካላት እንዳስቸገሯቸው መግለጻቸው አይዘነጋም። የኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎች ያለፈውን ጭቆና ረስተው በከፍተኛ ምቾት ላይ በመሆናቸው ‹‹የሰፊውን ሕዝብ የኑሮ ሁኔታ ይገነዘቡታል፤ ችግሩ ይገባቸዋል›› ማለት እጅግ ያስቸግራል። በዚህ እጅግ የተንደላቀቀ ሁኔታ ላይ ያሉ ከበርቴዎች በነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ተወዳድረው ሥልጣን ሊያስረክቡ ይችላሉ ወይ?

በዘመነ አብዮት ሥልጣን ለምርጦች ብቻ መሆን የለበትም የሚል ጥያቄም ነበር። ይህም ትክክለኛ ጥያቄ ነበር። ችግሩ በዘመነ ኢሕአዴግ መልኩን ቀይሮ ‹‹ሥልጣን ለምርጣውያን›› የሚለው መርሆ በሰፊው የሚሠራበት ዘይቤ መሆኑ ነው። ዛሬ በአገራችን በብሔረሰብ ተዋጽኦ ስም ሥልጣን የሚይዙት ከየብሔረሰቡ የተወጣጡ ታማኝ አገልጋዮች መሆናቸውን ማንም ያውቃል። ሥልጣንና መወለድ በእጅጉ የተቆራኙበት ዘመን አሁን መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። እነኝህ ምንም ይኼ ነው የሚባል አቅም ሳይኖራቸው የአንድ ብሔረሰብ አባልና ታማኝ ካድሬዎች በመሆናቸው ብቻ ከወረዳ ባለሙያነት ተነስተው እስከ ሚኒስትር ደረጃ የደረሱ ሰዎች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚቆሙበት ዕድል አለ ወይ?

የኢሕአዴግ መሪዎች ለመድበለ ሐሳብና ለመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ያላቸው ቁርጠኝነት እጅግ አጠራጣሪ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም በብዙ መልኩ የሚገለጽ ነው። ወደ ከበርቴነት ከመቀየራቸው በፊት እንዲጸድቅ የታገሉለትን ሕገ መንግሥት በተለያዩ ዝርዝር ሕጎች መሸርሸር ከጀመሩ ቆይተዋል። በተለይ ከምርጫ 1997 ዓ.ም. ወዲህ ደግሞ በጣም ተባብሶ ቀጥሏል። በአንድ በኩል ሕገ መንግሥቱን በሌሎች ዝርዝር ሕጎች ያቅቡታል። ከዚህ ውጪ ደግሞ ፖሊሲዎችን በመጠቀም ብዙ ዕቀባዎች ይደረጋሉ። ለምሳሌ አገዛዙ የልማታዊ መንግሥትን ፈለግ እንደሚከተል ካወጀ በኋላ ቅድሚያ ለኢኮኖሚያዊ እድገት ልማት በመስጠት ሌላውን ወደ ጎን ገሸሽ የማድረግ ወይም ከዚያም አልፎ አገዛዙን የሚተቸውን ሁሉ በፀረ-ልማት በመክሰስ ማሳደድ እየተለመደ መጥቷል።

ኢሕአዴግ በስትራቴጂ ሰነዱ ላይ እንዳብራራው በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት የቀረቡት አማራጮች ሁለት ብቻ ናቸው። ሕዝቡ ወይ ኢሕአዴግ የሚከተለውን ‹‹ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አማራጭ መደገፍ ወይ ደግሞ የኪራይ ሰብሳቢና የፀረ ዴሞክራሲ አማራጮችን መምረጥ ይኖርበታል›› ይላል ኢሕአዴግ። ሕገ-መንግሥቱ የዜጎችን (በነጻነት) የመደራጀት መብት ቢደነግግም፣ አገዛዙ በፖሊሲ ሰነዱ ከእርሱ ውጪ ያሉትን ሁሉ በኪራይ ሰብሳቢነትና ፀረ ዴሞክራሲያዊነት ፈርጆ ሊያጠፋቸው ሲሰራ ቆይቷል። አገዛዙ አንድ ጊዜ አብዮታዊ ዴሞክረሲ ሌላ ጊዜ ልማታዊ መንግሥት ሌላ ጊዜ ደግሞ የአውራ ፓርቲ ሥርዓት ወዘተ እያለ ተቃዋሚ ድርጅቶችን በልዩ ልዩ መንገድ ከጥቅም ውጪ አድርጓቸዋል።

በዘመነ ደርግ አገዛዙን ሂስ የሚያደርጉና የሚቃወሙ ዜጎች ሁሉ በፀረ አብዮተኛነት፣ በገንጣይነት፣ በኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኛነት ወዘተ. ይፈረጁ ነበር። ደርግ ራሱን የአብዮቱ ብቸኛ አዋላጅና ጠባቂ አድርጎ ስለሚቆጥር ተቀናቃኝ ኃይሎችን የሚታገስ ኃይል አልነበረም። የኢሕአዴግን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው፣ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን ተቀብያለሁ የሚል ድርጅት ሆኖ ሳለ ተቀናቃኞችን መታገስ አለመቻሉ ነው። አሁንም ተቃዋሚ ድርጅቶች ልዩ ልዩ ታርጋ ይለጠፍባቸዋል። ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ ፀረ ዴሞክራቶች፣ የሻዕቢያ ተላላኪዎች፣ የቀለም አብዮት አራማጆች፣ አተራማሾች ወዘተ. እየተባሉ ይፈረጃሉ። በሚያሳዝን ሁኔታ በቅርቡ በጎንደርና በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰውንና የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የጠፋበትን ተቃውሞ በቅጡና በሰከነ ሁኔታ ፈትሾ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ በፀረ ሰላም ኃይሎች ሲሳበብ ተመልክተናል።

አገዛዙ በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዘመናት በተነጻጻሪ ሆደ ሰፊና ‹‹ዴሞክራት›› እንደነበር ከ1997 ዓ.ም.ብሔራዊ ምርጫ በፊት ይታተሙ የነበሩትን የሕትመት ውጤቶች ማየት ብቻ ይበቃል። ከነጉድለታቸው አገዛዙን የሚተቹ በጣም ብዙ ጋዜጦችና መጽሔቶች ነበሩ። በሰብአዊ መብትና በዴሞክራሲ ዙሪያ የሚሠሩ ብዙ ሲቪክ ማኅበራትም ነበሩ። ያ ሁሉ ተስፋ ሰጪ ጅምር ነው በምርጫው ማግስት በሚያሳዝን ሁኔታ የተቀጨው። ከዚያ ወዲህ ያለውን ሁኔታ ደግሞ ማንም ያውቀዋል። በተለይ ከምርጫ 2002 ዓ.ም. ወዲህ ደግሞ ድርጅቱ አውራ ፓርቲ መሆኑን ካወጀ በኋላ ለሂስና ለተቃራኒ አመለካከቶች ያለው አስተያየት ሲበዛ አሉታዊ መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚያ ወዲህ፣ ሕዝቡን አሸብሮ ለመግዛት የሚያስችል የፀረ ሽብርተኝነት ዐዋጅ ወጣ። ሲቪክ ማኅበራቱን የሚያኮላሽ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሕግ ወጣ። ሌሎችም አሳሪ ሕጎች ተቀፈቀፉ። በአጠቃላይ ድርጅቱ ከ1997ቱ ብሔራዊ ምርጫ ሰፊ ‹‹ትምህርት›› በመቅሰሙ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡ መብቶችን የሚሽሩ ሕጎች ማውጣትና ተቀናቃኞችን መቅጨት ልማድ ሆነ።

ለማጠቃለል፣ የአገራችን ፖለቲካ እጅግ አስቸጋሪና አስፈሪ ቅርቃር ውስጥ ገብቷል። አገዛዙ አንድ ለአምስት አደረጃጀት፣ የልማት ሠራዊት፣ የሴቶች ማኅበራትና ሊጎች፣ የወጣቶች ማኅበራትና ሊጎች ወዘተ እያለ በየቤቱ እየገባ፣ ጋዜጠኞች በተለያየ መንገድ እንዲፈሩና አገራቸውን ጥለው እንዲሄዱ እያዋከበ፣ ሲቪክ ማኅበራትን እየዘጋ ወዘተ. ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቸኛና ተገዳዳሪ የሌለው ኃይል እየሆነ ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች በበኩላቸው አገዛዙ ከሚያደርስባቸው ተጽዕኖ በተጨማሪ ውስጣቸው ያልጠራና ብዙ የቤት ሥራ ያለባቸው አካላት ናቸው። ሕዝቡም እንዳየነው ፖርቱጋሎች ከአንቶኒዮ ሳላዛር አገዛዝ በኋላ ጭቆናን አንታገስም እንዳሉት ወይም ስፔናውያን ከፍራንኮ አገዛዝ በኋላ ለመብታቸው እንደታገሉት ወይም እንደ ጋናና ሜክሲኮ ሕዝብ ጭቆናን ከመታገል ይልቅ በተለያየ መልኩ ተከፋፍሎ ለአንድ ጨቋኝ አገዛዝ ተመቻችቶ ተቀምጧል። ሕዝቡ ይህን እጅግ አደገኛና ለማንም የማይበጅ ሁኔታ ተገንዝቦ መብቱን ለማስከበር በኅብረት እስካልተንቀሳቀሰ ድረስ ጭቆናው መቀጠሉ ደግሞ ግልጽ ነው። ጭቆናን መርሳት ብቻ ሳይሆን በጭቆና ውስጥ መኖርን የተለማመደ ሕዝብ እጅግ ያስፈራል።

## ነጻ አስተያየት



አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)

# እድገቱ ለማነው?

## አስደናቂ እድገት ወይስ ተከታታይ ድህነት?

## (፫ - የመጨረሻ ክፍል)

ድሃ፤ ኋላ ቀርና የእርዳታ ጥገኛ በሆነችው ኢትዮጵያ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት የድሎት ኑሮ አሰቃቂውን የሕዝብ ኑሮ አያንጸባርቅም። የዚህ ጽሑፍ መሠረት የአሁኑ የእድገት ውጤት የገቢና የሀብት የተዛባ ሥርጭት ከቀጠለ ለብዙ ተከታታይ ትውልዶች የተዛባ ኑሮ፣ አለመረጋጋት፣ ጥልቀት ያለው ድህነት፣ አስፈላጊ ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብት ይገባኛልነት እና ከእነዚህ ጋር የተያያዘ የእርስ በርስ ግጭትና ከአሁኑ የባሰ ስደት ይፈጥራል የሚል ነው። የማንኛውም የበለጸገና በማደግ ላይ የሚገኝ አገር መንግሥት ትኩረት ለተወሰኑ ባለ ሀብቶች ተጨማሪ ገቢና ሀብት ለማበርከት አይደለም። ጥረት የሚያደርጉት በተቻለ መጠን የአብዛኛው ሕዝብ ገቢ እንዲጨምርና የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ እንዲሻሻል ነው። በቀላል አነጋገር፤ ገቢ ጨመረ፤ ኑሮ ተሻሻለ ሲባል ዋናው መስፈርት የአብዛኛው ሕዝብ ሕይወትና ኑሮ ተሻሻለ ማለት ነው። ይኼን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ የኢኮኖሚው መርህ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ሲሆንና የሕዝብ አገልጋይ የፖለቲካ አመራር ሲኖር ነው።

ይህም ማለት፤ በቀን አንድ ጊዜ ምግብ የሚበላው ሦስት ጊዜ ምግብ ለመብላት ቻለ ማለት ነው። ለሕይወት አደጋዎችን የሚያስከትል ውኃ የሚጠጣው የንጹሕ ውኃ አገልግሎት አገኘ ማለት ነው። በሽታ የሚያስከትል መጸዳጃ ይጠቀም የነበረው ዘመናዊ ወይም የተሻሻለ የመደዳኛ አገልግሎት አገኘ ማለት ነው። ደካማ መጠለያው ጎጆ የነበረው ዘመናዊ ቤት ለመግዛት ወይም ለመከራየት ቻለ ማለት ነው። ጤንነቱ ሲታወክ የረባ አገልግሎትና መድኃኒት ለማግኘት አቅም የሌለው ዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት አገኘ፤ አስፈላጊውን መድኃኒት ለመግዛት ቻለ ማለት ነው። ገቢው እነዚህን ለሕይወት ወሳኝ የሆኑ ፍላጎቶች ካሟላ በኋላ፤ አንዳንዴም እያሟላ፤ ልጆቹን ለማስተማር ቻለ ማለት ነው። ዘመናዊ የመገናኛ አገልግሎት ለመጠቀም ቻለ ማለት ነው። ቀስ በቀስ መኪና ለመግዛት ቻለ ወዘተ ማለት ነው።

ይህ ነው አንድ አገርን የማኅበረሰባዊው እድገት ሰፊና ጥልቀት ያለው ነው፤ የመካከለኛው መደብ በግልጽና በሚታይ ደረጃ እየተስፋፋ ነው የሚያስብለው። አንድን አገር አደገ የሚያስብለው ከቁንጮው ላይ ያለው ትንሽ የሀብታሞች መደብ አይደለም። ሙባረክና ቤተሰቦቹ ሀብታም ስለነበሩና በድሎት ይኖሩ ስለነበረ የግብጽ ሕዝብ የተሻሻለ ኑሮ ይኖር ነበር ማለት አይደለም። እያደጉ ሄዱ በሚባሉት ወይም መካከለኛ ገቢ አላቸው በሚባሉት አገሮች የመካከለኛው መደብ እያደገ፤ እየሰፋና ብሔራዊ እየሆነ ስለሄደ የፍጆት ዕቃና አገልግሎት ፈላጊው እያደገ ይሄዳል ተብሎ በባለሞያዎች ይነገራል። ስለዚህ፤ በኢትዮጵያ እድገት አለ ማለቱ ብቻ የአገሪቱን ማኅበረሰባዊ ጤናማነት አያሳይም።

ዛሬ፤ በነጻ ገበያ የሚያምኑ ሆነ በልማታዊ መንግሥት ሚና አግባብነት፣ ለሕዝብ ሕይወት፣ ለሰላም፣ ለመረጋጋት እና ለዘላቂ እድገት ተቆርቋሪ የሆኑ መሪዎች (የካቶሊኩን ፓፓስ፤ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቱን የበላይ መሪ) ጨምሮ በተደጋጋሚ የሚያሳስባቸው ጉዳይ የገቢና የሀብት በጥቂት ግለሰቦችና ቤተሰቦች የበላይነት መያዛ ሁለት አደጋዎችን እንደሚያሳይ ነው። አንደኛው አደጋ ‹‹አይ ሲስ››፣ አልሸባብና አልቃይዳ ለመሳሰሉ ጠብና ግጭት ጫሪ እንቅስቃሴዎች መሠረት መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው፤ የእድገት ውጤት ለጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎች ጥቅም ብቻ ከዋለ ማንኛውም አገር የማምረትና የሥራ ዕድል የመፍጠር ኃይሉ ደካማ መሆኑ ነው። ሁኔታው ሥር ከሰደደ በኋላ ለመመለስ የማይቻል መሆኑንም ያሳስባሉ። ለዚህ መፍትሔ ብለው የሚያቀርቡት ሐሳብ ለሕዝብ የሚገዛ የፖለቲካ፣ የማኅበረሰብና የኢኮኖሚ መርህን ነው።

በጥቂቶች ኪራይ ሰብሳቢዎችና በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ መካከል በግልጽ እየሰፋ የሄደው የገቢ፤ የሀብትና የድሎት ኑሮ ልዩነት አደጋን እንደሚፈጠርና ድህነትን ወደማይበገር ደረጃ እንደሚያደርሰው ግልጽ ነው። አሁን ባለው የገቢና የሀብት ሥርጭት ከቀጠለች፤ ኢትዮጵያ ወደ መካከለኛ ገቢው ክበብ ለመግባት የምትችል አይመስለኝም፤ ብትችል እደሰታለሁ። እንዲያውም የእርስ በርስ ግጭት ጥልቀት ይይዛል የሚል ስጋት አለኝ። የሌሎችን የወደቁ አገሮችን ምሳሌ አድርጌ ብወስድ፤ የተዛባ ገቢና ኑሮ ከአገዛዝ ጭካኔ ጋር አብሮ ሲከሰት ለሽብርተኞችና ለሕዝባዊ አመጽ መንስኤ ይሆናል። በአገዛዙ የተጠቀሙ ጥቂት የተያያዙ ቡድኖች የያዙትን ሀብት ለመጠበቅ ሲሉ ጭካኔ የተሞላበት፤ ለብዙ ዜጎች ሕይወት እልፈት ምክንያት የሚሆን ግድያ ያካሄዳሉ። በአገዛዙ እምነት የሌላቸው ሀብታቸውን ማውጣት ይጀምራሉ። በአገር ሆኖ መታገሉ አያዋጣም የሚል ግምት ስላላቸው የሚመርጡት መሸሽን ነው። ሀብት ያለው መደበቂያ ስለማያጣ መግቢያውቸው ብዙ ነው። መግቢያ የሌለው ተራውና ድሃው ኢትዮጵያዊ ይሆናል። አዲስ ባለሀብቶች አገራቸውን ትተው የሚሸሹበትን ምክንያት ሲሰጡ፤ ሰላምና እርጋታ ከሌለ እድገት አይኖርም፤ ያካበትኩት ሀብት አስተማማኝ አይደለም፤ በሚል እምነት ነው። በተመሳሳይ፤ ገዢው ፓርቲ የሚናገረው እርጋታና ሰላም ከሌለ ተጠቃሚው ሕዝብ ይጎዳል ነው። የሚሸሹትም ሆነ የሚገዙት ከእድገቱ ሰላሙና እርጋታው ለማን ጥቅም እንደሚውል በግልጽ አይናገሩም፤ ሊናገሩም አይችሉም።

ዛሬ በሶሪያ፤ ቀደም ሲል በሶማሊያ እንዳየነው ሕዝብ አገሩን እየለቀቀ ልክ እንደ ጎርፍ ሌሎችን አገሮች ያጥለቀልቃል። የሥራ ዕድል እንደተፈለገው አለመኖር፤ ከመጥፎ አገዛዝና ከእርስ በርስ ግጭት ጋር ሲጣመር ከእሳት ላይ ቤንዚን እንደመጨመር ይሆናል። ስደቱን ያባብሰዋል ማለቴ ነው። በወገኑ ጨክኖ ወገኑን ለሽያጭ ከሚያቀርብባቸው አገሮች ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች። የችግሩ መሠረት አገዛዝና የሥራ ዕድል ማጣት ስለሆነ ሥርዓቱ ካልተለወጠ የሰው ንግድ አይቆምም ማለት ነው። አውሮፓ ማኅበር ያቀረበው ዘገባ ያመለከታቸው የስደትና የሰው ንግድ ምክንያቶች አሉ። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገዛዝ ዜጎቹ ተሰድው የውጭ ምንዛሬ እንዲልኩ ያደርጋል። የሚገፋው ሥርዓቱ ነው፤ የሚስበው ሥራና ደሞዝ ማግኘቱ ነው።

ሌሎቹ የስደት መንስኤዎች ይጠቀሳሉ። የሰብአዊ መብቶች መገፈፋቸው፤ የእርስ በርስ ግጭቶች፤ የሃይማኖት ግጭቶች (በክርስትናና በእስልምና ተከታዮች መካከል)፤ የመሬት ነጠቃ፤ አለመረጋጋትና ጦርነቶች ይገኙበታል። ይኼን ግዙፍ ችግር ለመፍታት የጋራው ማኅበር፤ ኢትዮጵያንና ኤርትራን ጨምሮ 23 አገሮችን የሚያካትት የሁለት ቢሊዮን ዶላር ባጀት ፈሰስ ያለው ፕሮግራም አዘጋጅቷል። ምን ለማድረግ? በኢትዮጵያና ተመሳሳይ አገሮች የሥራ ዕድል ለመፍጠር። የሥራ ዕድል መፍጠሩ አግባብ አለው። ሆኖም የውጭ እርዳታ ከጥገኝነት ባሻገር ፖሊሲያዊና መዋቅራዊ ችግሮችን የፈታበት አገር አላውቅም። ችግሩ በውጭ እርዳታ ሊፈታ አይችልም። ‹‹ዓባይን በጭልፋ›› እንደሚሉት በኢትዮጵያ ብቻ በዓመት ቢያንስ ሁለት ሚሊዮን የሥራ ዕድል መፈጠር አለበት። የግል ክፍሉ ካልፋፋና ካልተስፋፋ፤ ፓርቲውና መንግሥት ተመጣጣኝ የሆነ የሥራ ዕድል ለመክፈት አይችሉም። በየትኛም እድገት የሚያሳይ አገር፤ 90 በመቶ የሚሆነውን የሥራ ዕድል የሚፈጥረው የግሉ ክፍል ነው። ይኼን ግዙፍ እድል የሚፈጥረው የመካከለኛውና ከፍተኛው የግል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው። የውጭ ኢንቬስተሩ አይደለም፤ አገር ተከል ወይንም አገር ወለድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ነው።

በኢትዮጵያ የወጣቱን ስደት እያባባሰው የሄደው የሥራ ዕድል አለመኖር ብቻ አይደለም። የሰብአዊ መብቶች፤ የማኅበረሰባዊ፤ የኢኮኖሚያዊና ሌሎች መብቶች መረገጥ፤ የእርስ በርስ ግጭት፤ ሁኔታውን አባብሰውታል። አፈናው ሲጨምር ስደቱም ይጨምራል። እርግጥ፤ ስደተኞቹ ተሰደው ገቢያቸው እያደገ ሲሄድና ከኑሯቸው የተረፈ ገንዘብ ሲያጠራቅሙ ለስደት ያበቃቸውን አገዛዝ ሙጥኝ ብለው አንድ ኮንዶ፤ ወይም ቪላ ወይም ሌላ ይገዛሉ። ኮንዶውን በመግዛታቸው ለስደት ያበቃቸውን ሥርዓት ያሞግሳሉ። አንዳንዶቹ የአገራቸውን ግዛታዊ አንድነት፣ ነጻነት፣ ክብርና ሉዓላዊነት፤ የሕዝባቸውን ተፋቅሮና ተሳስቦ መኖር በኮንዶው ይለውጣሉ። አገርን በኮንዶ ለመለወጥ ከሚቻልበት ደረጃ እንዴት ደረስን? የሚሉ ታዛቢዎች እሰማለሁ። አገዛዙ የሚፈልገው ይኼን ነው። ‹‹ኑ! አገራችሁን አልሙ፤ ቤት ሥሩ ወዘተ.›› እያለ ስደተኛውን ደጋፊ ለማድረግ ያላደረገው ጥረት የለም። በአንድ በኩል ስደተኛው ከአገሩ ጋር ያለው እትብት ጠንካራ ስለሆነ ኢንቨስትመንቱ አግባባ አለው ለማት ያስችላል። በሌላ በኩል በኢንቬስትመንቱ ዙሪያ የሚመጣውን ማኅበረሰባዊ ቀውስና የከተማ መሬትና የቤት ግንባታ ዋጋ እየናረ መሄድ በአንክሮ አልተመለከተውም። የዜግነት መብቱን ለመጠቀም አልቻለም፤ አልደፈረም። ይኼ ሁኔታ ያስከተለው አመለካከት አለ። አንዱ፤ ለአገሩና ለመላው ሕዝብ ደህንነት የሚያስብ ለምን ጠፋ? የሚል ጥያቄ በተደጋጋሚ መሰማቱ ነው። ሁለተኛው፤ የፓርቲውና የሥርዓቱ ባለሥልጣናት ስግብግብነት ወደ ሌላው የማኅበረሰብ ክፍል፤ በተለይ ወደ ስደተኛው ተዛምቷል የሚል ነው።

በእኔ ግምት፤ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት ሥርዓቱ የፈጠራቸው ሁኔታዎች ናቸው። የእኔ ትውልድ የከፍተኛ ትምህርት ስደተኛ፤ ውጭ ተምሮ ወደ አገሩ የሚመለስ ኢትዮጵያዊ ከሁሉ በላይ የሚመኘው የተማረውን ትምህርት ለአገሩ ዘመናዊነት ለመጠቀም ነበር። አገሩ ካደገች ራሱም እንደሚጠቀም ያውቃል። መጥፎውን የውጭ ባህል ከጥሩው የመለየት ችሎታና ፍላጎት ነበረው። ሁሉን ነገር አያግበሰብስም ነበር።

ኮንዶውን ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም በላይ አምልኮ የሚኖረው ግለሰብ ወይንም ቤተሰብ የማያጤነው ነገር አለ። ይኼውም፤ አገር ከሌለ፤ የእርስ በርስ እልቂት ከተካሄደ፤ ፍትሕ ከሌለ ሰላም እንደማይኖር፤ ሰላም ከሌለ ኮንዶው ሊወድም እንደሚችል ነው። አዲሱ ተጠቃሚ፤ ‹‹እድገቱ ለማነው?›› የሚለውን ጥያቄ አላሰበበትም ማለት ነው። አሁን በአገራችን የተከሰተው ሁኔታ ፍትሕ አለመኖሩን ያሳያል። ፍትሕ ስለሌለ ሰላው ከፍተኛ ቢሆንም ሕዝቡ ከሸፈተ ቆይቷል። ይኼ ክፍተት አሁን ሕዝባዊ እየሆነ ሄደ እንጂ ችግሩ ከተከሰተ ቆይቷል። ተቃዋሚው ክፍል በምርጫ ዘጠና ሰባት ‹‹ለማሸነፍ›› የቻለበት ዋና ምክንያት መብቶች ስለታፈኑ፤ ዕድሎች ስለታፈኑ፤ ጎሳዊ አድልዎ ስላየለ፤ ኪራይ ሰብሳቢነት ተቋማዊ እየሆነ ስለሄደ ነው። ሕዝቡ የአገዛዝ ሥርዓት ለውጥ እንደሚፈልግ አሳይቶ ገዢው ፓርቲ የሕዝቡን ድምጽ ቀለበሰው። አሸናፊ የሆነው ተቃዋሚም ብልሃት የተሞላበት አመራር አላሳየም። አገርና ወገን ተረሳና፤ ግብግቡ የሥልጣን ሆነ። በአጠቃላይ ሳየው ግን፤ ሁኔታው ታፈነ እንጂ ችግሩ አልተፈታም፤ ለእውነተኛ ዴሞክራሳዊ አገዛዝ ያለው ፍላጎት ከሕዝቡ እእምሮ አልወጣም። በጎንደርና በኦሮምያ የሚከፈለው መስዋዕት የዚህን ፈለግ የተከተለ ነው።

በቅርቡ በጎንደርና በኦሮሚያ እንዳየነው ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ የሆኑ ግዙፍ ችግሮች ገጥመዋታል። ሕወሓት በበላይነት የሚያሽከረክረው ኢሕአዴግ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት አላወቀውም፤ ቢያውቀውም ይክዳል። የሚቆጣጠረው የመገናኛ ብዙሃን የሚያንጸባርቀውም ይህንኑ ነው። አማራም ሆነ ኦሮሞ ወይም ሌላ ሕዝብ እንዲሁ ላምጽ ብሎ አይነሳም። ከጀርባው ቀስቃሽ ከሌለው ጎረቤት ጎረቤቱን አይገድልም። አብሮ፣ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ በአንድ ቤተክርስቲያን ጸሎት አድርጎ፣ ቀብር ሲሆን አብሮ አልቅሶ፣ ደስታ ሲሆን አብሮ ዘፍኖ የሚኖረውን የጎንደር ሕዝብ አማራና ቅማንት ብሎ መከፋፈል በራሱ የተከሰተ አይደለም። ከጀርባው ሆኖ የጥንት ዘር ከመሬት ቆፍሮ ያወጣውና ወጣቶችን አሰልጥኖና ድጉማ ሰጥቶ ሕዝብ ከሕዝብ እንዲገዳደል ያደረገው ኃይል ሕወሓት መሆኑን ብዙ ታዛቢዎች ጽፈውበታል። የእኔት እምነት አማራውና ቅማንቱ ከፋፋዩን ኃይል  በውል ሲገነዘብና ለራሱ የወደፊት ዕድልና ሕይወት ሲል መተባበሩ አይቀርም። አሁንም እንደሚታየው የቅማንትና የአማራ ጎንደሬዎች በአንድ ድምጽ አትከፋፍሉን፤ እርስ በርሳችን አታጋጩን፤ ከእነጭራሹ ተውን፤ ችግሮቻችን ራሳችን በጋራ እንፈታለን እያሉ ነው። ወንድም ከወንድሙ፤ ጎረቤት ከጎረቤቱ ጋር ሲጋጭ እርጋታና ልማት አይታሰብም እያሉ ነው። መሬታችን ለሱዳን አትስጡብን፤ ከሰጣችሁ ራሳችን መስዋዕት አድርገን ዳር ድንበራችን እናስከብራለን እያሉ ነው። ሰሚ ግን አላገኙም። ሊያገኙም አይችሉም። ችግሩን ሆነ ብሎ የፈጠረው በከፋፍለህ ግዛው የሚያምነው ሕወሓት ስለሆነ ሥርዓቱ ካልተለወጠ ችግሩ አይፈታም። በአጭሩ፤ አሁን እንደምናየው ሁሉም እየተጎዳ ነው። የሁሉም ሕይወት እየተናጋ ነው። በጎንደርም ሆነ በኦሮሚያ፤ ሕወሓት/ኢሕአዴግ የሚነግረን ችግሩን የፈጠረው የክልሉ አመራር ስለሆነ ችግሩን መፈታት ያለበት የክልሉ አመራር ነው የሚል ተንኮል የተሞላበት ብሂል ነው። በአማራውና በኦሮሞው ክልል የበላይ ካድሬዎችን፤ የራሱን ርዕዮት፤ የራሱን ራዕይና የራሱን ምኞት በሚያንጸባርቅ መልክ ያሰለጠነውና ድጎማ ሰጥቶ ተወላጁ ካድሬ የራሱን ወገኖች እንዲያፍን፤ እንዲገድልና እንዲያሳድድ የሚያደርገው የሕወሓት ጠባብ ጎሰኛና ብሔርተኛ ቡድን መሆኑ የታወቀ ነው። አዲስ ነገር አይደለም።

ብዙ ጊዜ ሲወራ የቆየው ፕሮፓጋንዳ አማራውና ኦሮሞው በማይታረቅ ጥላቻ ዑደት ውስጥ ገብቷል የሚል ነው። ይኼ የከፋፍለህ ግዛው ስልት እስካሁን ሠርቷል። ሁለቱም ክፍሎች በጋራ ሆነው በዋናው የአገዛዝ ችግር ላይ እንዳያተኩሩ አድርጓቸው ቆይቷል። በቅርቡ የተከሰተው ሕዝባዊ ተቃውሞ የሚያሳየው እንቅስቃሴ ይኼን ለሁለቱም ግዙፍ ቁጥር ላላቸው ሕዝቦች ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ የመጠቀም ኃላፊነቱ የሁለቱም ሕዝቦች ልሂቃን፤ ምሁራን፤ ልዩ ልዩ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

**ከጀርባው ሆኖ የጥንት ዘር ከመሬት ቆፍሮ ያወጣውና ወጣቶችን አሰልጥኖና ድጉማ ሰጥቶ ሕዝብ ከሕዝብ እንዲገዳደል ያደረገው ኃይል ሕወሓት መሆኑን ብዙ ታዛቢዎች ጽፈውበታል። የእኔት እምነት አማራውና ቅማንቱ ከፋፋዩን ኃይል በውል ሲገነዘብና ለራሱ የወደፊት ዕድልና ሕይወት ሲል መተባበሩ አይቀርም**

## ኢኮኖሚ

ጥበበ ሲራክ
(tibebes@hotmail.com)

# ጠበቃ የሚሻው የዜጎች የኢኮኖሚ ነጻነት

የኢኮኖሚ ነጻነት ዜጎች በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ በብሔረሰባቸው፣ በሃይማኖታቸው ወዘተ. አድልዎ ሳይደረግባቸው በነጻነት፣ በመረጡትና በፈለጉት የኢኮኖሚ መስክ በዕኩልነት እንዲሰማሩ (እንዲሳተፉ) የሚያስችል የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ነው::

የዜጎች የኢኮኖሚ ነጻነት በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 41 ‹‹የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህላዊ መብቶች›› ውስጥ የተካተተ ቢሆንም በተግባር ግን በአገራችን የኢኮኖሚ ነጻነት እጦት አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ብዙ መረጃዎች ያመለክታሉ::: ይህንን ከሚጠቁሙት መረጃዎች መካከል ‹‹ሄሪቴጅ ፋውንዴሽን›› እና ‹‹ዎል ስትሪት ጆርናል›› በተባሉ ተቋማት እ.ኤ.አ. ከ1995 ጀምሮ በየዓመቱ የሚወጣው የኢኮኖሚ ነጻነት መጠቁም (Economic Freedom index) ሪፖርት ዋነኛው ነው:: ይህ አሃዛዊ መለኪያ የሚያመለከተው ዜጎች በአገራቸው ውስጥ በነጻነት (በምርጫቸው)፣ ያዋጣኛል ባሉት የኢኮኖሚ መስክ ሀብታቸውንና ዕውቀታቸውን በመጠቀም፤ ሌሎችም ዜጎችም ይህንኑ የማድረግ መብታቸውን ሳይጋፉ የማምረት፣ የመሸጥ እና የመለወጥ መብትን ነው:: እነዚህ ተቋማት ይፋ ያደረጉት ግራፉ እንደሚያሳየው እ.ኤ.አ በ2013 እና 2014 ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጭቆና ካለባቸው አገራት ውስጥ ተካታለች:: በ2015 የወጣው የተቋማቱ ሪፖርት ደግሞ ኢትዮጵያን ከዓለም 149ኛ፤ ከሰሐራ በታች ካሉ 46 የአፍሪካ ወስጥ አገራት ደግሞ 37ኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል:: በዚሁ የ2015 ሪፖርት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ነጻነት ከሌለባቸው አገራት ውስጥ ተካታለት:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ሙስናና መድሎ እንደሆነ በሪፖርቱ ተጠቅሷል:: ሪፖርቱ የመንግሥት ባለሥልጣናት በከፍተኛ ሙስና ውስጥ የተዘፍቁ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ብድር፣ የመሥሪያ ቦታና የሥራ ቅጥር የሚያገኙት የገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች መሆናቸውን አስቀምጧል::

በመንደር ለማሰባሰብ እና ለልማት በሚሉ ምክንያቶች በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ያለፍላጎታቸው ከመሬታቸውና ከቀያቸው እንዲነሱ መደረጉ ኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት ነጻነት ከሌላባቸው አገረት ተርታ ያሳለፍት ሌላኛው ምክንያት እንደሆነ ይኸው ሪፖርት ያስረዳል:: ሪፖርቱ በመንግሥት የተጣለው የግብር ዓይነትና መጠን የዜጎችን የመስራት፣ የመቆጠብና ኢንቨስት የማድረግ አቅምንና ፍላጎትን በከፍተኛ ደረጃ የሚፈታተን መሆኑን በመጥቀስ ይህም አገሪቱን የምጣኔ ሀብት ነጻነት ካላቸው አገራት ግርጌ እንድትሰለፍ ማድረጉን አትቷል:: በእርግጥ ይህ ሪፖርት የግብር ሥርዓቱ የዜጎችን የኢኮኖሚ ነጻነት ያሳጣል ሲል የሚጠቅሰው የሥራ ቅጥር ግብር ጣሪያ 35 በመቶ እና የንግድ ሥራ ትርፍ ግብር 30 በመቶ መሆኑን ጠቅሶ ነው:: ይህንን ሪፖርት ያወጡት ተቋማት ሰፋ ያለ ጥናት አድርገው ቢሆን ኑሮ ውጤቱ ከዚህ የከፋ ይሆን እንደነበር መገመት አያዳግትም:: ለምሳሌ ያክል በቁርጥ ግብር ሥርዓት (Presumptive taxation system) በአነስተኛ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎች ሠርተውት የማያውቁትን የገንዘብ መጠን በግብር መልክ እንዲከፍሉ እንደሚጠየቁ፤ በዚሁም ምክንያት ንግዳቸውን ለመዝጋት እንደሚገደዱ፤ መንገድ ዳር ጫማ በመጥረግ የሚተዳደሩ ዜጎች በወር 12 ብር እንደሚከፍሉ (እንደሚቀሙ)፤ በሌላ በኩል ደግሞ በመቶ ሚሊዮን ብር እያንቀሳቀሱ ሰባራ ሳንቲም ግብር የማይከፍሉ ዜጎች መኖራቸው ግንዛቤ ውስጥ አልገባም::

ከዚህ በተጨማሪ በጀርመን የልማት ተቋም በዶ/ር ቲልማን አልቴንበርግ ተጠንቶ ‹‹Industrial Policy in Ethiopia›› በሚል ርእስ እ.ኤ.አ. በ2010 የታተመው ጽሑፍ መደምደሚያ ላይ ከደረሰባቸው ነጥቦች አንዱ የሚከተለው ነው::

Business and politics are still strongly entwined in Ethiopia ... party-affiliated endowments have taken many of the business opportunities left for private engagement. It is not always clear to what extent political considerations reflect the business strategies of those firms, and vice versa.” (pp. 29) ‹‹በኢትዮጵያ የንግድ ሥራና ፖለቲካ እርስ በርስ ተወታትበዋል ... የግል ኢንቨስተሮች ሊሰማሩባቸው የሚገቡ (የሚችሉ) አብዛኞቹ የሥራ ዘርፎች በፖለቲካ ፓርቲዎች የንግድ ድርጅቶች ተይዘዋል፤ የነዚህ በፖለቲካ ፓርቲዎች የሚተዳደሩት የንግድ ድርጅቶ ስትራቴጂ ነው የፖለቲካ ውሳኔን የሚወስነው ወይንስ የመንግሥት ፖለቲካዊ ውሳኔ ነው የንግድ ድርጅቶችን ስትራቴጂ የሚወስነው የሚለው ብዙ ጊዜ ግልጽ ሁኖ አይታይም::››

ይኸው ጥናት እንደሚያመለክተው የተወሰኑ ባለሀብቶች ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በንግድ ሽርክናና ሎሎች እንዲህ ነው ተብለው ሊጠቀሱ በማይችሉ (ለሕዝብ ግልጽ ባልሆኑ) ጥቅማጥቅሞች መተሳሰራቸውን ጠቅሶ፤ እነዚህ አካለት ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል የበለጠ የኢኮኖሚ ነጻነት እንዳላቸው ይገልጻል::


‹‹Business, Politics, and State in Africa: Challenging the Orthodoxies on Growth and Transformation›› በተሰኘው መድብል ውስጥ ተካቶ ‹‹Ethiopia: Rent-seekers and Productive Capitals›› በሚል ርእስ የወጣው የቲም ኬልሴል ጥናት ከላይ የተጠቀሰውን የቲልማን አልቴንበርግን መደምደሚ ያጠናክረዋል:: የቲም ጥናት የሕወሓት ንብረት የሆነውን የኤፈርት (EFFORT) አመሠራረትና ሒደት በስፋትና በጥልቀት ከተነተነ በኋላ ኤፈርትን በተለየ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች አይወሰኑም ማለት አይቻልም ሲል ይደመድማል:: ለቲም ከልሴል ጥናት ማረጋገጫ የሚሆነው የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ጋር ያደረጉት ቃለ መጠይቅ ነው:: በዚህ ቃለ መጠይቅ በጊዜው የኤፈርት ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ‹‹መለስ ከመሰዋቱ በፊት የአምስት ዓመት የትግራይ ኢንዱስትሪ በኤፈርት እንዴት መፈጸም እንዳለበት የጻፍው ስትራቴጂ ነበር›› ማለታቸው የአገራችን ፖለቲካ የሚያሳልፋቸው ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎች ለኤፈርት እና ኤፈርትን ለመሳሰሉ ተቋማት ያደሉ ናቸው ወደሚለው መደምደሚያ ይወስዳል::

በሌላ በኩል አክሴል ቦርችግሪቪንክ ‹‹Emerging Economies and Challenges to Sustainability: Theories, Strategies, Local Realities›› በሚል መድብል ‹‹Ethiopia: Rapid and Green Growth for All?›› በሚል ርእስ እ.ኤ.አ. በ2014 ባሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፍ ገዥው ፓርቲ የሚከተለውን የኢኮኖሚ ሞዴል ዜጎችን በእኩል ደረጃ ተሳታፊ ማድረግ እንደተሳነው አሳይተው ይህም በዜጎች መካከል ያለውን የገቢና የሀብት ልዩነት እንዳሰፋው አትተዋል::

ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች መረዳት እንደሚቻለው የገዥው ፓርቲ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና ደጋፊዎች በተሰማሩበት የንግድ ዘርፍ በነጻ ገበያ ሥርዓት ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ አዳጋች ነው:: በገዥው ፓርቲ ሥር ለተሰበሰቡት ነጋዴዎች የሚደረግላቸውን የተለየ መድሎን ተቋቁሞ ገበያ ውስጥ መዝለቅ የቻለ ነጋዴ የፖለቲካ ሥልጣንን ተገን ባደረገ አሻጥር (ማስፈራራትንና እስርን ይጨምራል) ከገበያ እንዲወጣ ይደረጋል:: ፖለቲካዊ ደባ ከተፈጸመባቸው ባለሀብቶች ውስጥ የኢተዮጵያ አማልጋ ሜትድ ሊሚትድ ባለቤት የነበሩትን አቶ ገብረየስ ቤኛን መጥቀስ ይቻላል:: አቶ ገብረየስ ተሰማርተውበት የነበረው ዋነኛው የንግድ መስክ በአሁኑ ወቅት በገዥው ፓርቲ ድርጅቶች (ጉና፣ አምባሰል፣ ወንዶ እና ዲንሾ) በሞኖፖል የተያዘው የማዳበሪያ ንግድ ነው:: አቶ ገብረየስ ቤኛ በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ESAT) ጋር ባደረጉት ሰፊ ቃለ መጠይቅ በፖለቲካ አሻጥር ለ1 ቢሊዮን 700 ሚሊዮን ብር ኪሳራ ተዳርገው በመጨረሻም የሐሰት ውንጀላና ዛቻ በመበርታቱ ንግዳቸውን ዘግተው በስደት ይኖሩባት ወደነበረችው አሜሪካ መመለሳቸውን አስረድተዋል::

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የኢኮኖሚ ነጻነት የግለሰብን ብሎም የሕዝብን ገቢና የኑሮ ደረጃን በየውቅቱ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋል:: የኢኮኖሚ ነጻነት በተከበረበት አገር ዜጎች ለሥራ ቅጥር የሚታጩት በትምህርት ደረጃቸው፣ በሥራ ልምዳቸውና በችሎታቸው ነው:: ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ነጻነት በታጣበት አገር ዜጎች ለስደት ይዳረጋሉ:: የዜጎቻችንን ሕይወት እየቀጠፈ ላለው ስደት ዋነኛው ምክንያት የኢኮኖሚ ነጻነት እጦት መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው:: የሥርዓቱ ባለሥልጣናት ‹‹ለዜጎች ሰደት መንስኤው የግንዛቤ እጦት ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሠርቶ መቀየር ይቻላል›› ሲሉ ድንበር በማቋረጥ ላይ ያሉ ዜጎች በበኩላቸው አገራችን ውስጥ ሠርተን መቀየር ይቅርና በነጻነት ሠርተን መብላት አልቻልንም በማለት ያማርራሉ:: የጀርመን ሬዲዮ የአማርኛው ፕሮግራም ክፍል ‹‹መፍትሔ የሚያሻው የስደት አባዜ›› በሚል ርእስ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም. ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ተሳታፊ የነበሩት ከሳውዲ ተመላሽ ኢትዮጵያዊ ይህንኑ ነው ያረጋገጡት::

የኢኮኖሚ ነጻነት ባልተረጋገጠባት አገር ሕዝቦች በእኩልነት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑበት ልማት ሊመጣ አይችልም:: የዜጎች የኢኮኖሚ ነጻነት ባልተከበረበት አገር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች (ነጻነቶች) ይከበራሉ ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው:: እንደዘርፉ ምሁራን ገለጻ ኢኮኖሚውን የተቆጣጠረና የሕዝቦችን የኢኮኖሚ ነጻነት የደፈጠጠ መንግሥት የሕዝብን ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ጭምር እንደተቆጣጠረ ይገልጻሉ:: ዜጎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነታቸውና ደጋፊነታቸው ሥራ የሚቀጠሩ፤ በፖለቲካ አመለካከታቸው ከሥራ የሚሰናበቱበት አገር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ይከበራል ተብሎ አያታሰብም:: ምርጥ ዘርና ማዳበሪያን ከገዥው ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች (ከጉና፣አምባሰል፣ ወንዶ እና ከዲንሾ) ብቻ እንዲገዛ የተገደደ አርሶ አደር የልቡን ይናገራል ተብሎ አይጠበቅም:: የኢኮኖሚ ነጻነት የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዳይሸራረፉ የሚረዳ ትልቁና ዋነኛው መደላድል ስለሆነ ፖለቲካኞችም ሆኑ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ተሟጋች ግለሰቦችና ተቋማት ለዜጎች የኢኮኖሚ ነጻነት ቅድሚያ ሰጥተው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል::




**ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የኢኮኖሚ ነጻነት የግለሰብን ብሎም የሕዝብን ገቢና የኑሮ ደረጃን በየውቅቱ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጾ ያደርጋል። የኢኮኖሚ ነጻነት በተከበረበት አገር ዜጎች ለሥራ ቅጥር የሚታጬት በትምህርት ደረጃቸው፣ በሥራ ልምዳቸውና በችሎታቸው ነው**

## ነጻ አስተያየት



ግዛቸው አበበ

# ኢሕአዴጋውያን ሆይ! ዕዳም አደጋም አለባችሁ

የታኅሣሥ 12 ቀን 2008 ዓ.ም. የቀለም ቀንድ ጋዜጣ እንግዳ ሆነው የቀረቡት አቶ አብርሐም ጌጡ የአገዛዙ ሰዎች ዘርፈው የሰበሰቡትን ሀብት ጥቅም ላይ ለማዋልም ቢሆን ዴሞክራሲና መረጋጋት አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆም የገዥው ቡድን ባለሥልጣናትና አውራ ሰዎች ቢያንስ ለራሳቸው ብለው አገሪቱ ወደ ክፉ አዘቅት ውስጥ እንዳትገባ ጥረት ማድርግ እንዳለባቸው አሳስበዋል። ይህ ልባሞች ልብ ሊሉት የሚገባ ልባም ሰው የሰጠው ምክር ነው። ‹‹ፎቅ ይሠራሉ አይኖሩበትም፤ ስንቅ ያከማቻሉ አይበሉትም›› የሚል ትንቢት በሚነገርበት ዘመን ላይ ነን።

እርግጥ ነው ገዥውን ቡድን የሚዘውሩት ጥቂት የሕወሓት ሰዎች መሆናቸው የታወቀ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ደግሞ ገዥው ፓርቲ አሉት የሚባሉት አባላት ወደ ሰባት ሚሊዮን መድረሳቸው ሲነገር ቆይቷል። ምንጮች እንዳጋለጡትና ገዥው ቡድን ደጋግሞ እንዳመነው ሙስናና ኪራስ ሰብሳቢነት ተንሰራፍቷል። መልካም አስተዳደርም ተንኮታኩቷል። መልካም አስተዳደር ጠፍትል ማለት አምባገነንነት ነግሷል ማለት ነው። ሙስናው ይሁን ኪራይ ሰብሳቢነቱ የሚገለጸው በየቀበሌው ባለው የተዛባ አሠራር፣ በዘመድና በጉቦ በመስራቱ ብቻ ሳይሆን በቢሊዮኖች የሚቆጠር የአገር ሀብት ወደ ውጭ በማሻገርና በውጭ እንዳለ እንዲቀር በማድርግም ነው። የዚህ ግዙፍ ገንዘብ ሽሽት እና በውጭ ሰምጦ መቅረት የገዥው ቡድን አሽከርካሪች በተናጠልና ቡድን ወደ ውጭ በሽሽት ወይም በስንብት የሚነጉዱበት ዘመን ሊመጣ ይችላል የሚል ጥርጣሬ መኖሩን ያመላክታል ሊባል ይችላል።

ስለዚህ የአቶ አብርሐ ጌጡ አባባል በጣት ከሚቆጠሩት የገዥው ቡድን አውራዎች ይልቅ ሚለዮኖች የገዥው ቡድን ተራ አባላትንና አነስተኛ ባለሥልጣናትን የሚመለከት ነው ማለት ይቻላል። እነዚህ የገዥው ቡድን ሰዎች ሰሞኑን በመታየት ላይ ያለውን ግጭትና ሁከት ነግ በኔ ብለው እንደ ትልቅ ዕዳ ካላዩት አደጋ በነሱ ላይም እያንዣበበ መሆኑን ሊረዱት ይገባል።

በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የአዲስ አበባንና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ ማስተር ፕላን የሚመለከት ተቃውሞ ነበር። በውጭ እና በውስጥ ሚዲያዎች ላይ በሰፊው የሚነገረው ማስተር ፕላኑን በመቃወም የተቀሰቀሰው አመጽና እሱን ተከትሎ የመጣው ግጭት፣ ሞት እና እሥራት ቢሆንም በሰሜን ጎንደር በመተማ አካባቢ በአማሮችና በትግራይ ተወላጆች መካከል ግጭት መቀስቀሱም በውጭ ሚዲያዎች ተዘግቧል። አቶ ጌታቸው ረዳም የተባሉት የገዥው ቡድን ከፍተኛ ባለሥልጣን ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ግጭት ስለመቀስቀሱ ገልጸዋል።

የተቃውሞው አካሄድና ገዥው ቡድን ተቃውሞውን የያዘበት መንገድ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ተቃዋሚ ቡድኖች ተቃውሞውን በገዥው ቡድን ሥልጣን ላይ ብቻ ያነጣጠረ አብዮት አስመስለው መጯጯሃቸውና ‹‹ወያኔ ጉድ ፈላበት›› እያሉ መዘባበታቸው ሲታይ ኢትዮጵያችን ወደየት እየሄደች ነው ያስብላል። ከሰሞኑ የተከሰቱት ግጭቶችና ችግሮች በጥሞና እና በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊታዩ የሚገባቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ናቸው።

በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰው ተቃውሞ በአንድ በኩል ማስተር ፕላኑን የሚቃወሙ ወጣቶች ከገዥው ቡድን ታጣቂዎች ጋር የተጋጩበትና ሕይወት የጠፋበት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከ30 ዓመታት በፊት በኦሮሚያ ምድር የሰፈሩ አማሮች ቤት ንብረታቸውን ያጡበት ግጭትም ነበረ። በደቡብ ምዕራብ ሸዋ በአመያ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ በርካታ የገጠር ቀበሌዎች በተካሄደው ግጭት ምክያት በአካባቢው ነዋሪ የነበሩ አማሮች ተባርረው፣ ቤት ንብረታቸው በእሳት ወድሞ ቦታው ባድማ እና የአመድ ክምር ብቻ የሚታይበት ሆኖ መቅረቱ ተዘግቧል። በዚህ ሕዝብ የማፈናቀልና ቤት ንብረት የማቃጠል ዘመቻ የአካባቢው ባለሥልጣናት ተሳታፊዎች የነበሩ መሆኑ፣ ተፈናቃዮች ያለ ሰብሳቢ ተበታትነው መታየታቸውና ሰብሳቢ ማጣታቸው ገዥውን ቡድን እና የኦሮሚያን መንግሥት ተጠየቂነት የሚያሳይ ነው።

የገዥው ቡድን ባለሥልጣናት በኦሮሚያ የተቀሰቀሰውን የተቃውሞ ሰልፍ መጀመሪያ ሁከት እና አሸባሪዎች የሚመሩት ግርግር አድርገው ሲነግሩን ቆይተው ሲያበቁ ቀጠል አድርገው ‹‹ሕዝቡን ከማወያየት ዘግይተናልና ሰልፉ ብቻ ሳይሆን በሰልፉ የሚስተጋባው ጥያቄው ተገቢ ነው›› ሲሉ ተሰምተዋል። ጥየቄውና ሰልፉ ተገቢ ነው ቢባልም ሌላ አጀንዳ ያላቸው ኃይሎች እጃቸውን በአገሪቱ ጉዳይ ውስጥ እንዲያስገቡ በር ከፍቷል እየተባለ መወንጀሉ ግን አልቀረም።

ባለሥልጣናቱና መንግሥታዊው ሚዲያ ተቃውሞውን የቀሰቀሱ ወይም የሚያራምዱ ናቸው ብለው ብዙዎቹን ወንጅለዋል። አሸባሪዎች ናቸው በማለት ግንቦት ሰባትንና ኦነግን፣ እንዲሁም ሥልጣን ያመለጣቸው ተቃዋሚዎች ናቸው በማለት ኦፌኮን ተጠያቂ ሲያደርጉም ተሰምተዋል። ሌላ ተጠያቂ የተደረገ ቡድንም አለ። ኢቢሲ ከሠራቸው ዜናዎች በአንዱ ‹‹የኦሮሚያው ክልሉን አምጽ የቀሰቀሱት ጉዳቸው እንዳይጋለጥ የፈሩ ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው›› ሲባል ሰምተናል። ከዘገባው መረዳት እንደሚቻለው ጉዳዩ የኦሕዴድ ባለሥልጣናትን የሚመለከት ነው። መቼም እነ ዶ/ር መረራ ጉዲና የአዲስ አበባ ዙሪያን መሬት ቸብችበውና ኪራይ ሰብሳቢ ሆነው መሬቱ ወደ አዲስ አበባ ሲካተት ጉዳችን ይጋለጣል ብለው ይሰጋሉ አይባልም።

የሰሞኑን ግጭት በሚመለከት የአገዛዙ ባለሥልጣናት በመገናኛ ብዙሃናት ላይ ቀርበው ሲታዩ በገጽታቸውና በድምጻታቸው (በንግግራቸው ቃና ላይ) ልዩነት ይስተዋላል። በአቶ አባዱላ ገመዳ እና በኦሮሚያው ፕሬዘደንት ገጽታ ላይ ያረበበው ደመና በአቶ ጌታቸው ረዳ እና በአቶ ደመቀ ገጽታ ላይ የነበረውን ፍካት ስናነጻጽር በገዥው ቡድን ውስጥ በመጸነስ ላይ ያለ አንዳች ነገር መኖሩን ያመላክታል። ጉዳዩ የቆዳ ውፍረትንና የልብ ድንዳኔ ልዩነትን የሚያመለክት ወይም ‹‹ዘር ከልጓም ይስባል›› በሚለው ብሂል የሚገለጽ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ወይዘሮ አዜብ መስፍን ለወልቃይት ሕዝብ የሆኑትን ሆነው እንደተገኙት አባዱላ ገመዳም ለኦሮሞ ሕዝብ ሆነው የሚገኙ መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም። የአህያ ባል... ተብሎ የለ።

የኦፌኮው መሪ ‹‹አንድ ባለሥልጣን›› እያሉ ስም ሳይጠቅሱ ‹‹ወደዳችሁም ጠላችሁም የአዲስ አበባ የተቀናጀ ማስተር ፕላን ይተገበራል›› ብሎናል እያሉ በተደጋጋሚ ሲያወሱ አባዱላን ቀደም ብሎ ተነስቶ የነበረውን ተቃውሞ አስመልክተው ‹‹የተማሪዎች ተቃውሞ ተገቢ ነው ብለዋል›› እያሉ አሳጥተዋቸዋል ለማለት ይቻላል። ይህንን ተደጋጋሚ ማሳጣት ተከትሎ ከሁሉም የክልልና የፌደራል ባለሥልጣናት ቀድመው በመንግሥታዊ ሚዲያዎች ላይ በመቅረብ በኦሮሚያ ከተሞች ውስጥ የተቀሰቀሱ አመጾችን ለመተቸት ወይም ለመኮነን ቀዳሚነቱን አባዱላ እንዲወስዱ ተደርገዋል። በኢቢሲ አማርኛ እና ኦሮምኛ ፕሮግራሞች ላይ ቀድመው የታዩት እሳቸው መሆናቸውም አይዘነጋም።

ዘግየት ብለው ወደ ሚዲያ ላይ የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ‹‹የተመሰከረለት ዴሞክራሲ ባለበት አገር እንዴት እንዲህ ዓይነት ሁከት ይነሳል? ሐሳብን በሰላማዊ መንገድ መግለጽ ሲቻል እንዴት ልማት የሚያደናቅፍ ግርግር ይነሳል?›› ብለው ግራ የተጋቡ ለመምሰል ሲሞክሩ ታዝበናል። ለመሆኑ ገዥው ቡድን የተቃውሞ

የገዥው ቡድን ባለሥልጣናት ትልልቅ አገራዊ ወይም ክልላዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሕዝብ አይመለከተውም ወይም ሕዝብ ምን ያገባዋል ብሎ ማሰብና ነገሮችን ሁሉ ሸፋፍኖ ለማለፍ መሞከር <<ግመል ሰርቆ ጎንበስ...>> የሚባለው ዓይነት የማያዋጣና የማያዛልቅ ሽወዳ ከመሆን እንደማያልፍ ከዚህ ሊማሩ ይገባል

ሰላማዊ ሰልፍ ወዶና ፈቅዶ የመያስተናግደው መቼ ነው? ምን ሲፈጠርስ ነው? ገዥው ቡድን ሰልፎችን ገና ከጅምሩ ከማገድ አለፊ ከተባለ ፈቅዶ የተካሄዱ ሰልፎችን በፖሊስ ኃይል ከመበተን ጀምሮ በሚልካቸው ጋዜጠኞቹ እንከን ፈላልጎ ከመወንጀል የታቀበበት ጊዜ የለም። ይኸ ነው ሐሳብን በነጻ ለመግለጽ መፍቀድ የሚባለው?

የተመሰከረለት ዴሞክራሲ ሲባልስ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የታወሰው የባራክ ኦባማ ምስክርነት ይሆን? ባራክ ኦባማ የአሜሪካ ጥቁሮች ‹‹ባሪያ፣ ጦጣ፣ ችምፕ ወዘተ.›› እየተባሉ በዘረኛ ነጮች ብቻ ሳይሆን በፖሊሶች በገፍ እየተገደለ እያዩ ነገሩን ለመግታት እና ግፈኞችን ለፍርድ ለማቅረብ የረባ እንቅስቃሴ የማድርግ አስፈላጊነት ያልታያቸው ሰው ናቸው። ባለቤታቸው ሚሸል ኦባማ ተጽዕኖ አሳዳሪ ሴት ተብለው በታይም መጽሔት ሲመረጡ ለዚህ ምርጫ ያበቃቸው ከልክ በላይ ውፍረትን (Obesity) የመዋጋት ዘመቻ አካሄዱ ተብለው ነው እንጂ የአሜሪካ ጥቁሮችን መጠቃት ለማስቆም ወይም ለመከላከል ስለተንቀሳቀሱ አይደለም። ከዚህ ዓይነት ለራሱና ለወገኖቹ ክብርና ሕይወት የማይጨነቅ ቤተሰብ የሚገኝ ምስክርነት ጤነኛ አይሆንም።

የኢትዮጵያ ገዥ ቡድን ካሉበት በርካታ ችግሮች አንዱ የግልጽነት ድርቀት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እሱንና አገሩን የሚመለከቱ በርካታ ጉዳዮችን የሚሰማው ከውጭ ሚዲያዎች ነው። የኢትዮ-ሱዳን የድንበር ማካለል ጉዳይ፣ በጎንደርና በትግራይ መካከል ያለው የመሬት ውዝግብ፣ የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ወዘተ. በውጭ ሚዲያዎች ብዙ ሲባልባቸው የነበሩ ነገር ግን በኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሚዲያዎችና በባለሥልጣናቱ የማይወሱ ጉዳዮች ነበሩ። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ ነገሮች አብጠው ፈነዱና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ክልል ባለሥልጣናት በርብርብ የሚናገሩባቸው ጉዳዮች ሆነዋል። የገዥው ቡድን ባለሥልጣናት እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት በሚዲያዎች ላይ ለመናገር የተገደዱት ግልጽነት ያስፈልጋል በሚል እምነት ሳይሆን አመጹ ለሥልጣናችን አደጋ ያመጣል በሚል ስጋት ስላሳደረባቸው፣ እውነታውን ለማስተባበልና በየቦታው የተነሳውን አመጽ በውንጀላና በማስፈራራት ጸጥ ለማሰኘት ስለተፈጉ ነው። እዚህ ላይ አሳሳቢው ነገር የገዥው ቡድን ከፍተኛና ዝቅተኛ ባለሥልጣናት ለአገሪቱ በማሰብና ሕዝቦቿን በማክበር ግልጽነትን አለመለማመዳቸው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ መሬቱንና ድንበሩን በሚመለከት ዜና የሚያገኘው ሱዳን ትሪቡንን ከመሳሰሉ ሚዲያዎች ነው። ለምን? ከሕዝቡ ጀርባ በድብቅ የሚሠራ ጉዳይ ስላለ ይሆን?

የገዥው ቡድን ባለሥልጣናት ትልልቅ አገራዊ ወይም ክልላዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሕዝብ አይመለከተውም ወይም ሕዝብ ምን ያገባዋል ብሎ ማሰብና ነገሮችን ሁሉ ሸፋፍኖ ለማለፍ መሞከር ‹‹ግመል ሰርቆ ጎንበስ...›› የሚባለው ዓይነት የማያዋጣና የማያዛልቅ ሽወዳ ከመሆን እንደማያልፍ ከዚህ ሊማሩ ይገባል። የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ ሕዝብ ማንም ሊያታልለው አይችልም። ሕዝብ ለአጭርም ይሁን ለረዥም ጊዜ ዝም ይላል፤ ዝምታው ግን መታለል ወይም መፍራት አይደለም። ነገሩን ለማስተካከል የሚችለውን የቁርጥ ቀን ሰው፣ አመቺ መንገድና ጊዜ እስኪገኝ መጠባበቅ ብቻ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ አያቶች የወለዱኝ ከኢትዮጵያዊ ወላጆች የተገኘሁ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚሉ የገዥው ቡድን ባለሥልጣናት አባላት ብቻ ሳይሆኑ በሕገ መንግሥቱ ምክንያት በመፈቃቀድ አዲስ ኢትዮጵያዊ የሆንኩ ሰው ነኝ የሚሉ ባለሥልጣናት ተራ አባላት ሁሉ በጊዜ ሊያስቡበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

ሕዝብ ምን ያመጣል ብሎ ታንክና ወታደር በቤተ መንግሥትና በጽሕፈት ቤት ዙሪያ መደርደር በእንቧይ ካብ ለመመሸግ ከመሞከር ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታና ጊዜ ሊያመጣ ይችላል። ሕዝብን ከሕዝብ እያጋጩ መጫወትና በአገር ወሰንና ሉዓላዊነት መቆመር አደገኛ ነውና ለዚች አገር እና ለሕዝቦቿ እንቆረቆራለን የሚሉ የገዥው ቡድን ሰዎች ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ምንም ደንታ የሌላቸውንና ሕዝብ አያገባውም የሚሉ ጓዶቻቸውን አደብ ለማስገዛት መታገል ይገባቸዋል።

አቶ ገብሩ አሥራት ‹‹ሉዓላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ›› በሚለው መጽሐፋቸው (ገጽ 243-247) በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የሕወሓት፣ የብአዴን፣ የኦሕዴድ፣ የደኢሕዴን አመራሮች (የየድርጅቶቹ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት) የአገርን ጥቅም በማስቀደም አቶ መለስ ዜናዊን በድፍረትና በኅብረት እንደተጋፈጧቸው፣ አቶ መለስ ሳይወዱ በግድ የብዙሃን ሐሳብ እንዲቀበሉ የተገደዱበት አጋጣሚ እንደነበር ገልጸዋል። በወቅቱ የኢትዮጵያ መሬት እንደተያዘ የጠረጼዛ ዙሪያ ጨዋታ እንዲቀጥል የሚያደርውንና በአሜሪካ ባለሥልጣናት የተዘጋጀውን ሰነድ ቅቡል ለማድረግ አቶ መለስ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ሰነዱ ወደ ሕወሓት፣ ብአዴን፣ ኦሕዴድ እና ደኢሕዴን ማዕከላዊ ኮሚቴዎች ቀርቦ ውይይት እንዲካሄድበትና ውሳኔ እንዲሰጥበት ተደርጓል። ብአዴንና ኦሕዴድ በሙሉ ድምጽ ሰነዱን ውድቅ ሲያደርጉት፤ ሕወሓት ውስጥ በ17 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ተቀባይነት አጥቶ በ13ቱ ብቻ ተቀባይነት አግኝቷል። በደኢሕዴን ውስጥ ደግሞ በ49 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ተቀባይነት ሲያጣ በ2ቱ ብቻ ተቀባይነት አግኝቷል። ከዚህ በኋላ ሰነዱ ወደ ኢሕአዴግ ምክር ቤት ቀርቦ 51 ለ 8 በሆነ ውጤት ውድቅ ተደርጎ፣ አቶ መለስም በየደረጃው ሽንፈታቸውን ተከናንበው ኢትዮጵያ የተወረረ መሬቷን ለማስመለስ ችላለች። በወቅቱ ከብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አንዱ የነበሩት አቶ ዮሴፍ ረታ ‹‹የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር የለገሙት አቶ መለስ፣ ጥቂት የሕወሓትና የደኢሕዴን ጓዶቻቸው ሥልጣኑን ይልቀቁ›› የሚል ጥያቄ በይፋ ማቅረባቸውም ይታወቃል።

አሁንም በዚች አገርና በሕዝቧ ላይ ያንዣበበው አደጋ ይቀለበስ ዘንድ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል ውስጥ የታየው የሕዝቦች ግጭት ወደ ከፋ ፍጻሜ ከማምራቱ በፊት ይገታ ዘንድ ኢትዮጵያዊነቱ ዘላለማዊ ክብሬ ነው የሚሉ የገዥው ቡድን ሰዎች ሴረኞችን በድፍረት የመጋፈጥ ታሪካዊ፣ ብሔራዊና ሕዝባዊ ዕዳ አለባቸው። ሕገ መንግሥቱ በቅጡ ሊፈተሽ የሚገባበት ጊዜ መሆኑን ቆም ብለው ማሰብም ይገባቸዋል።

## የዜጎች ድምጽ

ፕ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ ጅግሳ

# ለሱዳን ሊሰጥ ነው ስለተባለው መሬት

## (ምክር - ለበስ አስተያየየት)

የኢትዮጵያ መንግሥት ለሱዳን ሊሰጣቸው ነው የተባሉት አሁን በጎንደርና በቤንሻንጉል አካባቢ የሚገኙት የእነ ኦሜድላና ጋምቤላ መሬቶች በእውነት የማን ናቸው? ያለጥርጥር የኢትዮጵያ ናቸው። ለምን እንደዚህ እንዳልኩ ዝቅ ብዬ አስረዳለሁ። መሬቶቹ በታሪክ የሱዳን ነበሩና ለሱዳን ይሰጡ የሚሉት የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት መሬቶቹን ለሱዳን ለመስጠት የሚያቀርቡት ምክንያት ‹‹በሱዳን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ተወካይ የሆነ አንድ ሻለቃ የወሰን ምልክቱን የተከለው እዚያ አካባቢ ነው፣ ቀድሞ አፄ ምኒልክ በዚህ ተስማምተው፣ በኋላ ደግሞ አፄ ኃይለሥላሴ እና ደርግም ይህን አጽድቀውታል›› የሚል ነው። በሌላ አነጋገር፣ በታሪካዊ ምክንያት ነው። እዚህ ላይ አንድ አስቂኝ ታሪክ ታወሰኝ። አንድ እንግሊዛዊ ከሱዳን የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግሮ የዱር እንስሳና አውሬ ለማደን በሚል ፈሊጥ ሲዘዋወር ለስለላ ነው ብለው በጠረጠሩት የአገሬው ተወላጆች ተገድሎ እዛው ተቀበረ። ታዲያ ይህን ሰበብ አድርጎ አንድ እንግሊዛዊ መኮንን (ምናልባትም እላይ የተጠቀስው እብድ ሻለቃ) ያ አካባቢ በሞላ ለእንግሊዝ መንግሥት ሊሰጥ ይገባል፣ አለ። በምን ሒሳብ ተብሎ በአባ መላ (ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ) ተጠየቀ። አንድ የእንግሊዝ ዜጋ ሞቶ እዚህ ስለተቀበረ፣ ሲል መለሰ። አባ መላም ከትከት ብለው ስቀው፣ እሺ ደግ ነው፣ አንድ የእንግሊዝ ዜጋ ሞቶ እዚህ ስለተቀበረ ይኼን ሁሉ መሬት ለናንተ እንሰጣችኋለን። የአፄ ቴዎድሮስ ልጅ ልዑል ዓለማየሁ ለንደን ውስጥ ሞቶ እዛው ለንደን (ዌስትሚኒስቴር አቢ) ስለተቀበረ እኛ ደግሞ ለንደንን እንረከባችኋለን። በዚህ ከተስማማህ ውል መፈራረም እንችላለን፣ ብለው አሾፉበት። ከዚያ ቦታ በቅጽበት ዳብዛው ጠፋ።

ስለታሪክ ካወሳን ዘንድ፣ ይኼ ዛሬ ሱዳን የተባለው ምድር ሁሉ ቢያንስ ለ4000 ዓመታት ያህል የኢትዮጵያ ግዛት ነበር። ጥንት የሚታወቀው ኑብያ ተብሎ ነበር። ኖባ በተሰኘው የኩሽ ዘር ስም። መናገሻውም መርዌ ነበር። የዛሬ 2900 ዓመት ግን ሱዳን ይባል ጀመር። ይህ ስም የወረደው ከአፄ አክሱማይት እናት ከንግሥት ሳዶንያ ነው። እሱ በሕፃንነቱ የግብጽ ፈርኦን ሆኖ እስከሚያድግ ድረስ እስዋ በ350,000 የአማራ ሠራዊት ታጅባ ዙፋኑን እየጠበቀች በሱ ስም ግብጽን፣ ሊብያን እና የዛሬውን ሱዳን ታስተዳድር ነበር። በዚህ ምክንያት፣ ከሳሐራ በረሐ በታች ያለው ምድር በሞላ ሳዶንያ ተባለ። ቀስ በቀስ ደግሞ ሱዳን። እንዳውም ኑብያ ውስጥ የነበረው መርዌ ለዛ አካባቢ እንደ ዋና ከተማ ሆኖ ያገለግል ነበር። ቢያንስ 14 የኢትዮጵያ ሴቶች ህንደኬ በሚል ማዕረግ በንግሥትነት በተከታታይ ዛሬ ሱዳን፣ ግብጽና ሊብያ የሚባሉትን አገሮች ለ1000 ዓመት ያህል ገዝተዋል። ለመጨረሻ ጊዜ የኑብያ ንጉሥ የነበሩት በ16ኛው ክፍለ ዘመን የኖሩት አፄ ፋሲል ነበሩ። ከኑብያ ብቻ ሳይሆን ከስናር (ከካርቱም ብዙ ያልራቀ ስፍራ) ድረስ የወርቅ ግብር ይመጣላቸው ስለነበር አዝማሪ እንዲህ ሲል የሱዳን ገዥነታቸውን አረጋግጦላቸው ነበር፡-

ጎንደር ቢያጉረመርም ፋሲል ፈረስህ፣
ኑብያና ስናር ወርቁን ጫኑልህ።
ሳሩን ተጠየፈ የፋሲል ፈረሱ፣
ክምር የሱዳን ወርቅ ገፈራው ነው ለሱ።

‹‹ገፈራ›› ማለት የፈረስ ምግብ ነው። ዛሬ ፉርሽካ የምንለው ዓይነት። እንግዲህ ይህ ግጥም፣ ሱዳን እስከ የዛሬ 500 ዐመት የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረች ይመሰክራል። በሁዋላ በዘመነ መሳፍንት እና ከዚያ ትንሽ ቀደም ብሎ ኢትዮጵያ እየተዳከመች ስትሄድ ቱርኮች ያዝዋት። ቱርኮች ተዳክመው ለእንግሊዝ ለቀቁላት። እንግዲህ ከእጅ የወጣ አገር በታሪክ ሰነድ ወይም ማረጋገጫ የሚመለስ ቢሆን ኖሮ፣ መላው ሱዳን ለኢትዮጵያ በተመለሰ ነበር። ከላይ እንደ ተረዳነው ሱዳን የኢትዮጵያ እንጂ ኢትዮጵያ የሱዳን ሆና አታውቅም። ታዲያ በምን ምክንያት ነው አሁን የኢትዮጵያን መሬት የጠየቀችው? እስዋ አፏን ምን ቁርጥ አርጉዋት ጠየቀችና? እሷም በራሷ ተነሳስታ ደፍራ መሬት አለኝ አላለችም። አሁን በአመራር ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ደርግን በሚዋጉበት ሰዓት ሱዳን ለዋለችላቸው ውለታ ወሮታውን ሊመልሱላትና አሁንም ተቀዋሚዎቻቸውን እንዳታስተናግድ የሚከፍሉዋት ዋጋ መሆኑ ነው። ወዲህም መሬቱ ያለው በአማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላና በኦሮሞ ክልሎች ስለሆነ የእኛን ምድር ስለማይመለከት ችግር የለውም ዓይነት ነው። ብሔራዊ ስሜት የሚባል ነገር ስለሌለ። መሬት በነጻ እንካ ከተባለ ማን ይጠላል? ስለዚህ ሱዳኖቹ እየፈነጠዙ ሊወስዱ አኮብኩበዋል።

የኢትዮጵያን መሬት ለግሰናት በደቡብ ሱዳን የተወሰደባትን መሬት እንተካላት ካልተባለ በቀር።

ሰጭና ነሺው እንግሊዝ ከተደረገና የእንግሊዝ መንግሥት ለክቶ፣ ‹‹አበጥሮ››፣ ‹‹አንጥሮ›› ሁሉን አጣርቶ ራሱ በመጨረሻ ያረጋገጠው የሱዳን ምድር እላይ የተጠቀሰው ስፋት ከሆነ በምን ሒሳብ ነው እንግሊዝም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት የማያውቁትን የኢትዮጵያን መሬት በህቡዕ ለሱዳን የሚለገሳት? አይገባትም እንጂ በእርግጥ ሱዳን ይገባኛል የምትለው መሬት ካላት

> በመሆኑም ከኢትዮጵያ ልቀበል ይገባኛል ልትል የሚያስችላት ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ጥሪኝ አፈር የላትም። ስለ ኦሜድላ ብቻ እንኳዋን ብንዘክር፤ አፄ ኀይለሥላሴ በሱዳን በኩል ከስደታቸው ሲመለሱ ከ5 ዓመታት በሁዋላ ለመጀመሪይ ጊዜ የኢትዮጵያን ሰንደቅአላማ ሰቅለው የአውለበለቡት ኦሜድላ ላይ ነበር

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት 1600 ኪሎሜትር ለም መሬት ለሱዳን ይገባታል ብሎ ጠበቃ የቆመላት እላይ የተጠቀሰው ቅኝ-ገዢ መኮንን በቸከለው ድንበራዊ ችካል ክሆነና በእንግሊዝ ቅኝ ገዥነት አገር ቅርጫ እንዲሆን ከተፈቀደ፣ እንዲሁም እንግሊዝ ያቀናው መሬት ሁሉ ለሱዳን ይቸር ዘንድ ከተፈረደ፣ የቀድሞው የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች የነበሩት እነ ዩጋንዳና ሱዳን፣ ካስፈለገም እነ ናይጀሪያ ሁሉ ለሱዳን መሰጠት ይገባቸዋል ማለት ነዋ!!! የሆነ ሆኖ፣ ያ ዎፈፌ ቅኝተኛ እንግሊዝ ምኞታዊ ሕልም አልሞ የፈለገውን ያህል የወሰን ድንጋይ ቢተክልና አፄ ምኒልክም አልተስማሙም እንጂ ቢስማሙለትና መሬት ቆርሰው ቢሸልሙትም እንኳዋን ያ ውል የሞተ ነው። ለምን ቢባል፣ ሱዳንን ዓለምና የተባበሩት መንግሥታትም ያወቃትና በታሪኩዋ ለመጀመሪያ ጊዜ ራስዋን ችላ የራስዋን ባንዲራ ያውለበለብችበት ዳር ድንበር አሁን የአለው ነውና። እ.ኤ.አ. በ1953 ዓመተ ምህረት እንግሊዝ ግዛቴ ይኼ ብቻ ነውና ያንቺም ግዛትሽ ይኼው ነው ብሎ በዐሥር ጣቱ ፈርሞ የተወላት መሬት ነው። እሱውም ከመከፈሏ በፊት የነበረው የቆዳ ስፋቱ 2,505,813 ስኩዌር ኪሎሜትር የሆነው ነው። ከመከፈሏ በፊት ሱዳን በቆዳ ስፋት ከአፍሪካ አንደኛ ነበረች። አሁን ሦስተኛ ነች። አሁንም ከኢትዮጵያ ትልቃለች ማለት ነው። የያዘችው ይበቃት ነበር።

ወደ ተባበሩት መንግሥታት ሄዳ ነው እንጂ አቤቱታዋን የምታቀርበው በስርቆሽ በር ነው እንዴ መሬት ቆርሳ የምትሮጠው? ወይስ መሬቱን ከቦጨቀች በኋላ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ቀርባ መርቁልኝ ልትል ይሆን? እሷ ግን ወደ እዛ እስካሁን ያልሄደችው እ.ኤ.አ. በ1953 እንግሊዝ ካስረከባት በቀር ሌላ መሬት ስለማይገባት ‹‹ወይጅ ወዲያ አትቀልጅ!›› ይሉኛል፣ ብላ ፈርታ ነው። አለዚያ ሱዳን ነጻ ከወጣች ጀምሮ መሪዎችዋ ከኢብራሂም አቡድ ጀምሮ እስከነ ኑሜሪ እና አሁን ያለውም አል በሺር የይገባኛሉን ጥያቄ ገና ድሮ ባቀረቡ ነበር። ሰበብ ፈጥረን ስለቀድሞ ውለታዋ እና ተቀዋሚዎቻችንን ስለምትገታልን እንዲሁ በነጻ እንችራት ካልተባለ በቀር እንደ እውነቱ ከሆነስ ሱዳን፣ ‹‹ኢትዮጵያ ያዘችብኝ፣ ይገባኛል፣›› የምትለው አንዲት ስንዝር መሬት የላትም። ከቅኝ ግዛት ነጻ ከወጡ በኋላ የአፍሪካ አገራት በሞላ የያዙት ድንበርና ወሰን የቅኝ ገዥዎችቸው እነዚህ ናቸው፣ ብለው ያረጋገጡላቸውን ብቻ ናቸው። ስለዚህ ሱዳን ከሌሎቹ የአፍሪካ አገራት በምንም አትለይም።


በመሆኑም ከኢትዮጵያ ልቀበል ይገባኛል ልትል የሚያስችላት ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ጥሪኝ አፈር የላትም። ስለ ኦሜድላ ብቻ እንኩዋን ብንዘክር፣ አፄ ኀይለሥላሴ በሱዳን በኩል ከስደታቸው ሲመለሱ ከ5 ዓመታት በሁዋላ ለመጀመሪይ ጊዜ የኢትዮጵያን ሰንደቅአላማ ሰቅለው የአውለበለቡት ኦሜድላ ላይ ነበር። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜም የ እንግሊዝ የቅኝ ገዢ ትልቅ ባለስልጣናት ለሰንደቅ ዓላማዋ አክብሮት በተጠንቀቅ ቆመው መሬቱ የኢትዮጵያ መሆኑን ተቀብለው ይመለከት ነበር እንጂ ‹‹የሱዳን መሬት ላይ እንዴት ባንዲራ ያውለበልባሉ!›› ሲል በንጉሡ ላይ ቅዋሜ አላሰሙም። ኦሜድላ የኢትዮጵያ ለመሆንዋ ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ አለ? ታዲያ በምን ምክንያት ነው አሁን ይቺ ታሪካዊ ስፍራ ለሱዳን የምትሸለመው? ቀዳማዊ ኀይለሥላሴ ኦሜድላ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሲያውለበልቡ ጦሩን እንዲያቀነባብር በእንግሊዝ መንግሥት ተሹሞ አብሮአቸው በሱዳን በኩል የገባው ሜጀር ዊንጌትም ታዛቢ ሆኖ አጎናቸው ነበረ። ንጉሡን ተሽቀዳድሞ አዲስ አበባ የገባው ሎርድ ካኒንግሃምም እሳቸው ኦሜድላ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንዳውለበልቡ አሳምሮ ያውቅ ነበር። እነዚህም ሁለት ታላላቅ የእንግሊዝ መንግሥት ተወካዮች ኦሜድላ የኛ ናት አላሉም። የሆነ ሆኖ እውነት እንግሊዝ ከአፄ ምኒልክ ጋር ተዋውሎ ከነበር እሱው እንግሊዝ የመሬት ይገባኛል ጥያቄውን ያቅርብልን እንጂ ያልተዋዋልናት ሱዳን ምን አገባት? ከሱዳን ሳንዋዋል እንዴት ሱዳን የተዋዋልነው ይከበርልኝ፣ ልትል ትደፍራለች? ይህን ጥያቄ ሊያነሳ የሚችል እንግሊዝ ብቻ ነው። ነበርም። ግን እንግሊዞች አላነሱም። ምክንያቱም ቀላል ነው። የዚህ ዓይነት ውል ከአፄ ምኒልክ ጋር ስላተፈራረሙ። ተፈራርመው ቢሆን ኖሮ መጠየቅ ብቻ አይደለም፣ የተፈራረሙበት ቀለም ሳይደርቅ መሬቱን እጃቸው ያስገቡ ነበር። ስላልተፈራረሙ ይህን አላደረጉም። የሱዳንን ነጻነት እንግሊዞች ሲፈቅዱም የተባለውን መሬት የኔ ነበር ብለው ወደ ሱዳን አላዘዋወሩም። አሁን ያለውን መሬት ብቻ ነው ትተውላቸው የሄዱት። እሱም ለሁለት ተከፍሎባቸዋል። ከእንግሊዝ የተረከቡትን መሬት እንኳን በቅጡ መያዝ አቅቷቸው ‹‹የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች፣›› የተባለው ተረት በነሱ ላይ ተፈጽሞባቸዋል። የራሳችውን አጥብቀው መያዝ ሳይችሉ የኛን መሬት መከጀላቸው ማስቆጣት ብቻ ሳይሆን ያስደንቃል።

እንግዲህ እንግሊዝ ከአፄ ምኒልክ ጋራ መሬትን አስመልክቶ ላለመዋዋሉ ሦስት ማስረጃዎች አሉ ማለት ነው። አንደኛ የተባሉትን መሬቶች ቀደም ሲል እጁ ባለመክተቱ፣ ሁለተኛ ንጎሡ ኦሜድላ ላይ ሰንደቅ ዓላማችንን ሲሰቅሉ አለመቃወሙ፣ ሦስተኛ ሱዳንን ለቆ ሲሄድ ለሱዳን ከተወላት የተባበሩት መንግሥታይ ባፀደቀላት ዳር ድንበር ውስጥ እነዚህን ሁሉ የኢትዮጵያ መሬቶች በካርታም ሆነ በጽሑፍ ባለማካተቱ። በነዚህ ሦስት ማስረጃውች ምክንያት እሩቅ ሳንሄድ፣ ሰነድ ለማግኘት አፈር ሳንቆፍር እና ድንጋይ ሳንፈነቅል ምኒልክ እና እንግሊዝ አንዳችም የመሬት ውል እንዳልተፈራረሙ እናረጋግጣለን። ተፈራርመዋል የሚል እስቲ ሰነዱን ያቅርብልን!!! ደግሞም ቢፈራረሙም እንኩዋን ውሉ የቅኝ ገዥዎች ስለሆነና ምኒልክም ሆነ ማንኛውም መሪ የአትዮጵያ መሬት የግል ንብረቱ ስላልሆነ መሬት ለባዕዳን ሰጥቻለሁ ቢል አይጸናም።

አፄ ምኒልክ ተስማምተውበት፣ አፄ ኀይለሥላሴ እና ደርግ ያጸደቀውን ነው እኛ በተግባር የምናውለው፣ ሲል ኢሕአዴግ ደጋግሞ ተናግሯል። ይህን መሠረት በማድረግ እኔ ብዙ ምርምር አካሂጄ ሁለቱ አፄዎችና የደርግ ሊቀመንበር የነበሩት ኮ/ል መንግሥቱ ኀይለማርያም ለሱዳን መሬት ለመስጠት የተዋዋሉበት አንድም ሰነድ አላገኘሁም። ምክንያቱም ስላልነበረ። ስለ ሌለም። አሁን በሕይወት ያሉት ኮ/ል መንግሥቱም አንድም የዚህ ዓይነት ውል ከሱዳን ጋር እንዳልተፈራረሙ አበከረው መስክረዋል። ይልቁንም እኔ ያገኘሁት መረጃ፣ አውሮፓውያን መንግሥታት ለብቻቸው ተሰብስበው አፍሪካን ለመቀራመት ያደረጉትን ውል ለአፄ ምኒልክ ነግረው የኢትዮጵያን ነጻነት ግን እንደሚያስጠብቁ በገለጹላቸው ጊዜ እሳቸው በሌሉበትና ባልተሳተፉበት ሁኔታ የተደረገውን ውል እንደማይቀበሉት በአጽንኦት አስገነዘቧቸው እንጂ አልተቀበሏቸውም። ጆሮ ያለው ይስማ። ልብ ያለው ልብ ይበል።



ማስታወሻ



ነብዩ ሲራክ

# በሕክምና ስህተት ዐሥር ዓመት የተኛው ኢትዮጵያዊ

**በኢትዮጵያዊው ብላቴና መሐመድ አብድልአዚዝ የሳውዲ መንግሥት የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት አጣሪ ቡድን ያረጋገጡት ግፍ ተፈጽሞ ውሳኔውን ዳር የሚያደርስ የመንግስት ተወካይ እጦት ዜጎች ላለፉት ዓመታት በዘገየው ፍትሕ አሳር መከራቸውን በማየት ላይ ናቸው**

ከምኖርበት ጅዳ ወደ ሳውዲ ዐረቢያ ወደ ዋና ከተማ ሪያድ ካቀናሁ ሳምንት ሆኖኛል:: ያ እንደ እሳተ ነበልባል የሚጋረፈው የሪያድ የበረሐ ሙቀት በለየለት ብርድና ቅዝቃዜ ተቀይሯል:: በሪያድ ቆይታየ ከኩባንያው ሥራ ውጭ በግል የምከታተለው ብርቱ ጉዳይ ቀጠሮም አለኝ:: የብላቴናው ኢትዮጵያዊ የመሐመድ አብድልአዚዝ ጉዳይ:: መሐመድ የዛሬ ዐሥር ዓመት ገደማ ጅዳ በሚገኝ ዶ/ር ሱሌማን ፈቂ በተባለ ሆስፒታል ውስጥ በተከሰተ የሕክምና ስህተት የተጎዳ ኢትዮጵያዊ ታዳጊ ነው::

በሪያድ ጉዞየ ዐሥር ዓመት ፍትሕ የተነፈገውን፣ ርትዕ የጎደለበትን ኢትዮጵያዊ ብላቴናና የወላጆቹን አበሳ የሳውዲ መንግሥትም ሆነ በኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ዘንድ እንዲታወቅ አሳዛኙን ታሪክ ይፋ ለማድረግ ነው:: በዚህ ጉዳይ በታዋቂዎቹ የዐረብ ኒውስና የሳውዲ ዐረቢያ ጋዜጦች ዝርዝር ጉዳዩን ከብዙ ድካም በኋላ ማሳካት ብችልም ያለፍኩበት መንገድ ቀላል አልነበረም:: ከወራት በፊት ከታዋቂው የዐረብ ቴሌቪዥን ‹‹MBC-1›› አዘጋጆች ጋር ያደረግኳቸውን ውይይቶች ተከትሎ በአካል ለመነጋገር ጭምር የአሁኑ የሪያድ ጉዞዬ ጥሩ አጋጣሚ ነበር:: ከአዘጋጆች ጋር የሚኖረን የውይይታችን ዋና ዓላማ ኢትዮጵያዊው ብላቴና ለ10 ዓመት ፍትሕ ተነፍጎት ተሸፋፍኖ ከተቀመጠነት የሳውዲ ከፍተኛ መንግሥት ኃላፊዎች እንዲያውቁት ጣቢያው በሚያቀርበው አንድ ልዩ ፕሮግራም እንዲቀርብ ማመቻቸት ነበር:: ይሁን እንጂ ቀጠሮዬን አክብሬ የተገኘሁ ቢሆንም የቴሌቪዥን አዘጋጆችን ማግኘት አልተቻለኝም:: ምክንያታቸ ‹‹የሥራ ብዛት አለብን ቀጠሮ ቀይረህ ና›› የሚል ቢሆም የሆስፒታሉ ባለቤቶች ረዥም እጅና ከፍተኛ የግንኙነት መረብ ጉዳዩ እንዳይታወቅ የሠሩት ሥራ ጥረቴን እንዳሰናከለው ሳልጠረጥር አልቀረሁም:: በታዋቂዎቹ የሳውዲ ጋዜጦችና በዐረብ ኒውስ ጋዜጣ ለማስዎጣት ለወራት የደከምኩት ድካምና እንግልት ልምድ አለኝና የቴሌቪዥኑ አዘጋጆች የማያሳምን ምላሽ ምንም አልመሰለኝም:: እናም ቀጣይ ቀጠሮ ይዘን ተለያየን::

ታኅሣሥ 15 ቀን 2008 ዓም ከመሐመድ እናት ሐሊማ የስልክ ጥሪ ደረሰኝ:: ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ብየ ስልኩን ሳነሳ ብርቱዋ እናት ሐሊማ በእንባ እየታጠበች ልጇ መሐመድ ዘጠኝ ዓመት ከተኛበት የሆስፒታል ክፍል ያለፈቃዷ እንደቀየሩት እያለቀሰች ነገረችኝ:: ‹‹አሁን እየወሰዱት ያለው እርምጃ ሀዘኔን አብዝቶታል፤ እስከ ዛሬ ለብቻው ክፍል ነበረው፤ የተሻለ ነገር ባይደረግለትም የሚከታተል ረዳት ሐኪምና ለብቻውም ክፍል ነበረው፤ ዛሬ ግን ያለ ምንም ዓይነት ሕክምና እርዳታ ከሌላ ታካሚ ጋር ቀላቅለውታል፤ በደል በዝቶብኝ አዝኛለሁ ነብዩ›› አለችኝ ሐሊማ እያለቀሰች::

የሚያሳዝነው ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ጉዳዩን መከታተል የጀመረው በጅዳ የኢትዮጵያ ቆንስል ኃላፊዎች ከዚህ ቀደም እናት በግፍ ከሆስፒታል ስትባረር ምንም ማድረግ አለመቻላቸው አልበቃ ብሎ ዛሬ የብላቴናውን መሐመድ ሕይወት ያመሰቃቀለው ሐኪም ቤት እንዳሻው ሲያደርግ ማስቆም አለመቻላቸው ነው:: በሕግ የተያዘው የመሐመድ ጉዳይ ቢያንስ ያለወላጆችና ቆንስል ኃላፊዎች ፍቃድ ከቦታ ቦታ መቀየር ባልተገባቸው ነበር:: ተወካዮቻችን ያኔ እናት ሐሊማ ከሆስፒታሉ ስትባረር ‹‹ደብዳቤ ጽፈናል›› ከማለት አልፈው ምንም ማድረግ አልቻሉም:: እናም እንደ አገር ዲፕሎማት ተንቀዋል:: የተወካይ ዲፕሎማቶቻችን ተሰሚነት ማጣት ከዚህ ቀደም የሐኪም ቤቱን ድፍረትና ንቀት መግታት የፈተነ የመብት ማስከበር ሥራ ባለመሠራቱ እንጂ ሌላ አይደለም:: ብላቴናው መሐመድ ከነበረበት ቦታ ሲቀየር የጅዳ ቆንስል ምላሽ ‹‹እርምጃውን በመቃዎም ደብዳቤ ጽፈናል›› ቢሆንም የእነሱን ደብዳቤ ግን ከቁም ነገር የሚቆጥረው አልሆነም። ይህ መሆኑ እየታወቀ የኢትዮጵያ መንግሥት ተወካዮች ለምን ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ የሳውዲ መንግሥት ሕግ አውጭ፣ አስፈጻሚ አካላትም ሆነ ወደ ፍርድ ቤት እንደማያደርሱት ለማንም ግልጽ አይደለም::

እርግጥ ነው የጅዳ የኢትዮጵያ ቆንስል መሥሪያ ቤት 9 ዓመታት በወላጆች እርዳታ ተጠይቆ ምላሽ ባይሰጥም ዘንድሮ አንባሳደር ውብሸት ከመጡ ወዲህ ወጉ ደርሶን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ጉዳዩን እየተከታተሉ ወደ ፍርድ ቤት እንደሚያቀርቡት ነግረውን ነበር:: ይሁን እንጂ ዛሬ ከ6 ወር በኋላ የተባለው ሁሉ መጨበጫ የሌለው መሆኑን ለመታዘብ ችለናል:: ላለፉት 6 ወራት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የጅዳ ቆንስል ጉዳዩን ለሳውዲ መንግሥት አቅርቦ ውሳኔ ያላሰጠበት እንቆቅልሽ እዚህ አድርሶናል:: ጉዳዩን በፍርድ ቤት ለማስያዝ ጠበቃ አቅርበን ‹‹የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን ሕጋዊ ምክር ለመጠየቅ የተላከው ደብዳቤ አልመጣም›› በመባሉ እነሆ ላለፉት ሁለት ወራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምላሽ አለመምጣት ሌላ ጉዳዩን በከፍተኛ ደረጃ ጎትቶታል::

## ለመሆኑ ሕፃን መሐመድ አብድልአዚዝ ማን ነው?

የ4 ዓመት ደልዳላ እያለ ድክ ድክ እያለ ሮጦ ለቀላል ሕክምና ከጅዳ ቆንስል መሥሪያ ቤት ፍንጫ ሥር በሚገኝ አንድ ሆስፒታል ገባ:: ብዙም ሳይቆይ ከሰመመን መንቃት አልችል አለ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከሰመመን አልነቃም:: በሐኪሞች ስህተት ብላቴናው መሐመድ ሕይወቱ ተሰናክሎ ላለፉት 9 ዓመታት የአልጋ ቁራኛ ነው::

ላለፉት ዐሥር ዓመታት በተቃረበው ጊዜ ከጅዳ ቆንስል ኃላፊዎች ጀምሮ ሳይኖር ‹‹አለሁ›› እስከሚለን የሴቶች ማኅበር ተወካዮች ለመሐመድ ፍትሕን ያስገኙ ዘንድ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦ ፍትሕ ማስገኘት ቀርቶ ጉዳዩ እንዲታወቅ አላደረጉም:: እናም ተበዳዮች ፍትሕ ርቋቸዋል:: የመሐመድ አብድልአዚዝ ቤተሰቦች ለ9 ዓመታት ደጋግመው ያደረጉት ውትወታ የጅዳ ቆንስል ኃላፊዎች ተቀባይነት አግኝቶ ባያውቅም ከሰባት ወራት በፊት ለአምሳደር ውብሸት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አገኘና በጉዳዩ ላይ ክትትል መጀመሩን ተመለከትን:: የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ቆንስል መሥሪያ ቤቱ ጉዳዩን በያዘው ማግስት ለ9 ዓመት የዋለለው የፍትሕ ጥያቄ መልስ አገኘ። በአሳር በመከራ ባደረግኩት ውትወታ ለመሐመድ ቤተሰቦች 2.4 ሚሊዮን የሳውዲ ሪያል ካሳ እንደሚሰጥ በሳውዲ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በተዋቀረው አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔው ተላለፈ:: ውሳኔው ባይከፋም ለሰዓታት ከመተንፈሻ መሣሪያ ውጭ መንቀሳቀስ የማይችለው ብላቴ ቤተሰቦች የተወሰነውን ካሳ ተቀብለው ከሐኪም ቤቱ እንዲለቁ የተላለፈውን ፍርደ ገምድል የወላጅ ቤተሰቦች ተቃወሙት:: በውሳኔ አሰጣጥ ሒደቱ ላይ የተገኙት የጅዳ ቆንስል ተወካይም የወላጆችን ውሳኔ በመደገፍ የውሳኔውን ፍትሐዊ አለመሆን ሳይቀበሉ ቀረ። ውሳኔ ያሳለፈው ኮሚቴ በሕክምና ስህተት መሐመድ በደል የደረሰበት መሆኑን የሚያረጋግጠው ሰነድና ሙሉ ውሳኔ በዐሥር ቀናት ውስጥ ለወላጅና ለቆንስል መሥሪያ ቤቱ ሰጥቶ ይግባኝ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መውሰድ እንደሚቻል ገልጾ ጉዳዩ ለጅዳ ቆንስል ተላለፈ:: ይህ የሆነው ልክ የዛሬ ስድስት ወር ነበር::

## ሕግ አስከባሪ የማጣት እንቆቅልሽ

ዛሬስ ? ዛሬ የተገባው ቃል የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ ጉም ሆኗል:: ቆንስል መሥሪያ ቤቱ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በኩል አቀርብኩት ያለው አቤቱታ መልስ አላገኘም:: ወላጆች ላፍታ ከመድኃኒትና ከሕክምና ውጭ መቆየት የማይችለውን መሐመድን ይዘው እንዲወጡ እየተወተወቱ ነው:: እንድትለቅ ተደርጋለች:: እናት ልጇቸውን በቅርብ እንዲያስታስታምም ከተሰጣት ማደሪያ በሆስፒታሉ ጸጥታ አስከባሪዎች እንድትለቅ ተደርጋለች:: ይህ ሲደረግ ለቆንስል መሥሪያ ቤቱ ቢያመለክቱም መጠለያውን ከመልቀቅ አልታደጓቸውም:: ይባስ ብለው ባሳለፍነው ሳምንት ታህሣሥ 15 ቀን 2008 ዓ.ም. ብላቴናው መሀመድ ላለፉት 10 ዓመታት ለተቃረበ ጊዜ ይኖርበት ከነበረው ክፍልና የሕክምና ይዞታ እንዲርቅ ተደረጓል:: በኢትዮጵያዊው ብላቴና መሐመድ አብድልአዚዝ የሳውዲ መንግሥት የጤና ጥበቃ መሥሪያ ቤት አጣሪ ቡድን ያረጋገጡት ግፍ ተፈጽሞ ውሳኔውን ዳር የሚያደርስ የመንግስት ተወካይ እጦት ዜጎች ላለፉት ዓመታት በዘገየው ፍትሕ አሳር መከራቸውን በማየት ላይ ናቸው:: በሪያድ የኢትዮጵያ ኢምበሲም ሆነ የጅዳ ቆንስል መሥሪያ ቤት፣ የተላለፈውን የውሳኔ ሰነድ ተረክቦ ጉዳዩን ወደ ፍትሕ አካላት ማቅረብ ተስኖኗቸዋል። የጎደለባቸው ፍትሕ እንዲሰፍን ዛሬም ተገፊዋ ይጮሃሉ:: ‹‹ቁሱም ዝም መጽሐፉም ዝም!›› የሆነበት እንቆቅልሽ ግን አልገባን ብሏል::

## የሳውዲ ፍትሕ ሥርዓትና የእኛ ጉዳይ

በሳውዲ ፍትሕ ሥርዓት ከላይ በአጭሩ ለማሳየት እንደሞከርኩት በሆስፒታል ስህተት የተፈጸመውን ስህተት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ ከባድ በደል ተፈጽሞባቸው ቀርቶ በከባድ የሳውዲ መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች የተፈጸመ የሕግ ጥሰት የሚሸፋፍን የሕግ ሥርዓት ሳላለመኖሩ ብዙ መረጃ ማቅረብ ይቻላል:: የቀደመውን ትተን ባሳለፍናቸው ጥቂት ሳምንታት ታዋቂው የሳውዲ ጋዜጣ እንዳስነበበን በሳውዲ አየር መንገድ ተጓዠ የነበሩ ሁለት ታዳጊ ኢራናውያንን ደፍረው በተከሰተው ውጥረት ወንጀል መሥራታቸው የተመሰከረባቸው ሁለት የአየር መንገዱ የጸጥታ ሠራተኞች የአራት ዓመት እስራትና 1000 ጅራፍ ተፈርዶባቸዋል:: ብዙ ብዙ አብነት ማቅረብ ይቻላል:: በደል ተፈጽሞ ሕግ ፊት ቀረቦ ውሳኔው የማያዎላዳ መሆኑን በርካታ ጉዳዮችን አውቃለሁ::

ወደ ኢትዮጵያዊው ብላቴና መሐመድ ስንመለስ የምናገኘው ግን ሌላ ነው:: መብታቸውን የሚያስከብር ተወካይ የመንግስት አካል አጥተናል:: ጉዳዩ ጠያቂ አጥቷል:: ሕግ ፊት እንኳ የሚያቀርበው ጠፍቷል:: ስለሆነም የዜጎች መብት የሚያገባቸው አካላት የት አሉ ? ብለን እንጠይቅ ዘንድ እንገደዳለን::

ለተገፊው መሐመድ ፍትሕ ማግኘት ሁላችን ልንተጋ ግድ ይለናል:: ቢያንስ ጉዳዩን ወደ ፍትሕ አካል ይቀርብ ዘንድ ሁላችንም የቻልነውን እናደርግ ዘንድ አደራየ የጠበቀ ነው:: ተወካዮቻችን የግፉአንን እንባ በመጥረጉና መብትታቸውን በማስከበሩ ሰናይ ምግባር ቆመው አለማየታችን የምስኪኗ የመሐመድ አብድልአዚዝ እናት እንባ የሚነግረን እውነታ አይጠፋም :: ‹‹ስለ እውነት እንመስክርና የመጣው ይምጣ›› ማለትን ለደፈረ ባለፉት በርካታ ዓመታት በዋነኛነት የዜጎች መብት የቆሙት ተወካዮቻችንም ሆነ የሚያደራጇቸው ማኅበራት ድግስ እየደገሱ በስሙ ገንዘብ ከመሰብሰብ ያለፈ ሥራ ሠሩ ቢባል ለሕዳሴውን ግድብ አደረጉ የሚባለውን ድጋፍ ብቻ ነው የምናገኘው። ለአገር ግንባታ፣ ለልማትና ድንበር ተደፈረ ሲባል ለአገሩ ቀናኢነት የሚያሳየው ዜጋ የፍትሕን ጉዳይ ግን ዛሬም ተዘንግቷል:: ይህ በእጅጉ የሚያም፣ ሲነገሩት እንኳ መስዋዕትነትን የሚያስከፍል እውነታ ቢሆንም ነግ በኔ ነውና እኔ የምፈራው መከፈል ያለበት መስዋዕትነት የለም:: ከልጆቸ፣ ከሞቀው ቤቴና ከአባቢው የተረጋጋ ኑሮየ እሰናከል ይሆናል:: ይህ ሁሉ ግን እውነቱን በተጨባጭ መረጃ ከመናገር ላፍታም ያህል አይገታኝም :: እውነቱን ተናግረን ከመሸበት እንደር:: ስለ ፍትሕ መከበር እናገራለሁ።

እናንተም ተናገሩ:: የየራስ ፍርዳችሁን ስጡ:: እኔ እንዳገባኝ እናንተም ያገባኛል ካላችሁ የማቀርበውን ጭብጥ መረጃ፣ ስለ ሰብአዊ መብት መከበርና ስለ ፍትሕ መረጃውን እየተቀባበላችሁ አስተጋቡት :: የተነፈግነውን ፍትሕ ማግኘት እስክንችል። የእናት ፍቅርን የምታውቁትም ሆነ የማታውቁ፤ የእናት አንጀትን መላወስ ሕመም ጠልቆ የሚሰማችሁትም ሆነ ስሜቱን የማይገባችሁ፤ የምትወዱትን ነገር በግፍ ስለመነጠቃችሁ እያሰባችሁ ስለ መሐመድና ስለ ግፉአን ቤተሰቡ ፍትሕ ማግኘት አቤት ትሉ ዘንድ አደራ እላችኋለሁ:: በሳውዲ መንግሥት ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አጣሪ ኮሚቴ በሕክምና መሰናከሉ የተረጋገጠው የብላቴናው ጉዳትና የፍትሕ እጦቱ አንገሽግሾናል:: ብላቴናውና ቤተሰቦቹ ፍትሕ ይሻሉ:: የወገናችን ጉዳይ ያገባናል:: ፍትሕ እንሻለን:: ፍትሕ ናፍቆናል። ጉዳዩን ወደ ፍትሕ አቅርቡልን!

# እድገቱ ለማነው . . .

ስብስቦችና በተለይ ወጣት ትውልድ ነው፡፡ በእኔ ግምት የአማራውና የኦሮሞው ሕዝቦች ከሚለያያቸው ይልቅ የሚያቀራርባቸው ይበልጣል፡፡ የወደፊቷን ፍትሐዊ፤ ዴሞክራሳዊ፤ እውነተኛ እኩልነት ያለባትን፤ ሁሉም ተከብሮና ከድህነት ተላቆ በሰላምና በመከባበር የሚኖርባትን ኢትዮጵያ በጋራ ተወያይተው፤ ሌላውን ሳያገሉ ለመመሥረት ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ የፖለቲካ መሠረቱን፤ የወደፊትን የመንግሥት አቀራረጽ፤ አመራሩን፤ የቋንቋውንና ሌላውን ችግር ሁሉ በጋራ ለመፍታት ይችላሉ፡፡ የአሁኑ ዕድል እንዳያመልጥ ከተፈለገ የሁለቱም ክፍሎች ተቆርቋሪዎች መፈላለግ፣ መናበብ፣ መነጋገር፣ መወያየትና መደራደር መቻል አለባቸው፡፡ ይቻላል ካሉ ምንና ማን ሊያቆማቸው ይችላል?

ኢትዮጵያ ታላቅ አገር ናት፤ ጥሩና ሁሉን የሚወክል አገዛዝ ካላት ዘመናዊ የሆነ ታላቅ ኅብረተሰብ ለመመሥረት ትችላለች፡፡ ታላቋን አገር ታናሽ እንድትሆን ያደረግናት እኛው ልጆቿና በጎሳ የከፋፈለን አገዛዝ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በድርቅ ረኀብ በተደጋጋሚ የሚሰቃየው ዝናብ፣ ወንዝ፣ ለመስኖ የሚሆን ገና ያልለማ መሬትና ታታሪ ሕዝብ ስለሌላት አይደለም፡፡ አላት፡፡ መሠረታዊ ችግሯ የአገዛዝና የአስተዳደር መጥፎነት ነው፡፡ የድርቅ ሽነፈር እንዲሁ አይከሰትም፡፡ ተከታታይ ስደት እንዲሁ አይፈጠርም፡፡ ከድርቅ ቸነፈር ውጭ ሁሉም ሥርዓት ወለድ ናቸው፡፡ ጥሩ አገዛዝ ባለባቸው አገሮች፤ ለምሳሌ ሕንድና ቻይና፤ ድርቅ ቢከሰትም በቸነፈር የሚሞት ሕዝብ አይታሰብም፡፡ ሕወሓት በበላይነት የሚያሽከረክረው ኢሕአዴግ መብቴ ይከበር ብሎ በተነሳው ሕዝብ ላይ ግፍ ፈጽሟል፤ ግን ይክዳል፡፡ በየቀኑ ሕጻናት በቸነፈር እየሞቱ አይሞቱም ይላል፡፡ ችግሩን ራሴ እወጣዋለሁ ካለ በኋላ የዓለም ለጋሾችን እርዳታ ይጠይቃል፡፡ ይኼ በአገዛዙ በኩል ያለው ሁኔታ ሲሆን፤ ሌሎቻችንም ረኀቡንም ሆነ የሕዝቡን አመጽና እልቂት በአንድነት መነጽር አናየውም፡፡

አብረውና ተባብረው መሥራት የሚገባቸው ተቃዋሚዎች ተፈላልገው በብልሃት አንድ ላይ ስላልቆሙ አሁንም ወገኖቻችን በተናጠል እየሞቱ፤ እየታሰሩ፤ እየተሰደዱ፤ በቸነፈር እየተጎዱ ነው፡፡ በአንድነት ድምጽ አይሰማም የምልበትን ምክንያት በምሳሌ ላቅርበው፡፡ በጎንደር በእስር ቤት የታጎሩ እዚያው እንዲቃጠሉ፤ ለመሸሽ የሞከሩት የጥይት በረዶ እንዲርከፈከፍባቸው መደረጉና በኦሮሚያ የስምንት ዓመት ወጣት ሳይቀር መገደሉ የአረመኔነት አገዛዝ ምሳሌ ነው፡፡ በሰላም የሚኖረውን አማራ ከቀዬ ማባረር፣ መግደል፣ ማሳደድና ማዋረድ አረመኔነት ነው፡፡ በጎንደር ከተማ ኢትዮጵያዊያን በእስር ቤት ቃጠሎ ሲሞቱ ፈጥኖ አለመድረስና ይበላቸው ማለት የአረመኔነት ምሳሌ ነው፡፡ ብዙ ሽህ የኦሮሞ ወጣቶችን ሰላማዊ ሰልፍ ስላደረጉ በሽብርተኛነት ፈርጆ በገፍ ማሰር ጭካኔ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ያወግዘው የነበረውን የደርግ ጭካኔ በባሰ ሁኔታ እየቀጠለበት ከሄደ እርጋታና ሰላም አይኖርም፡፡ በተመሳሳይ፤ ከኅብረተሰቡ አንጻር ስመለከተው፤ እንደዚህ ያሉ ጭካኔዎች የተለመዱ መሆናቸው ራሳችንንም ወደ የሕሊና ጥያቄ ውስጥ አስገብተውናል፡፡ መቼ ነው በተናጠል ሳይሆን በጋራ አንዱ ወገናችን ለሌላውን ደግፎ የሚነሳው? ሌላውን ደግፎ የሚሞተው?

## ፍትሕ የጋራ ነው

በእኔ ስሌት፤ ባለመተባበር ምክንያት ሕዝቡ የሚከፍለው ዋጋ ከፍተኛና አደገኛ ነው፡፡ ሌላም ጉዳይ አለ፡፡ በእኛ ቸልተኛነትና መከፋፈል ምክንያት ለኢትዮጵያ መፈራረስ ትኩረትና ድጋፍ ለሚሰጡ የውጭ ኃይሎች ወንፊት አበርክተናል፡፡ ባሕርያችን ጭፍን፣ ግትርና ግለኝነት የተጠናወተው መሆኑ እየጎዳን ነው፡፡ ልንክደው የማንችለው ሐቅ አለ፡፡ ይኼውም የፖለቲካ ባህላችን ብሔራዊ ችግሮችን በውይይትና በድርድር ለመፍታት የሚያስችል ፈቃደኛነት፤ መተማመን፤ ችግሮችን በመነጋገር ለመፍታት መወሰንን ይጠይቃል፡፡ ይኼ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የትግሬ፤ የትግሬ ወይንም ሌላ ሕዝብ ወይንም ልሂቃን ጥያቄ አይደለም፡፡ ሁላችንም የምንመኛቸውና የምንጋራቸው የአገዛዝ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በሕግ ፊት የሁሉም ኢትዮጵያዊያን እኩልነትን፣ የሰብአዊ መብቶች መከበርን፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን በማንኛውም ክልል በክብርና በደህንነት የመኖር መብት መከበርን፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሚሳተፉበት ነጻና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫ ተካሂዶ ሕዝብ ድምጹ የሰጠበትና የተሳፈበት ዴሞክራሳዊ መንግሥት እንዲቋቋም የኅብረት ሥራ ማካሄድ የሚጠቅሙ ጉዳዮች ሁሉም ተቃዋሚ ክፍሎች ይነገራሉ፡፡ በእነዚህ የምንስማማ ከሆነ ተፈላልገን በአንድ ላይ ሆነን ለመወያየትና ለኢትዮጵያና ለዓለም ሕዝብ አማራጭ ለመስጠት የማንችልበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? ከነሳና ከሃይማኖት በላይ አስበን ይኼን ጥያቄ የመመለስ ታሪካዊ ግዴታ አለብን፡፡ ከላይ የአማራውንና የኦሮሞውን መተባበር አስፈላጊነት አስመልክቶ እንዳቀርብኩት፤ ሌላው የወደፊት ሥርዓት ጉዳይ በውይይት፤ በንግግር፤ በመተማመንና በድርድር ይፈታል፡፡ ይኼን ታሪካዊ ጥሪ ለመመለስ የሚችሉ የአማራ፤ የኦሮሞ፤ የትግሬ፤ የደቡብ፤ የአፋር፤ የአፏክ፤ የሶማሌ፤ የትግሬ ወዘተ. ልሂቃን፤ ሽማግሌዎችና አባቶች እንዳሉ አምናለሁ፡፡ ሕዝቡ የሚፈልገው መግባባትን ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ ሕዝብን ከሕዝብ የከፋፈለ መሆኑን አብዛኛው ተቃዋሚ ይቀበላል፡፡ ስለሆነም፤ ገዢውን ፓርቲ ብቻ መሰናክልና ማነቆ ማድረግ አግባብ የለውም፡፡ መጀመሪያ የተቃዋሚው ክፍል ሥራውን ይሥራ፡፡ የገዢውን ፓርቲ ፈቃድ የምንጠብቅ ከሆነ ችግሩ በምንም አይፈታም፡፡ ለምን?

ገዢው ፓርቲ የረባ ተቃዋሚ እንዳለ አይቀበልም፡፡ ከማፈን ባሻገር ሁሉንም እያስቀመና እየለየየ አፈራርሷቸዋል፡፡ ኅብረት እንዲፈጥሩ አይፈልግም፡፡ ሥልጣኑን ለመልቀቅ አይፈልግም፡፡ ትዕቢተኛና ትምክሕተኛ የሆነ አገዛዝ ሁልጊዜ የሚመካው በውይይትና በመደራደር ሳይሆን በመሣሪያ ኃይል ነው፡፡ በጀርባ ሆኖ ሕዝቡ የውስጥ ችግሩን እንዲፈታ የሚቀሰቅሰው በግጭት፤ በቀም በቀል፤ አንዱ ሌላውን እንዲፈራው በማድረግ ነው፡፡ የተቃዋሚው ክፍል ማድረግ ያለበት ለመላው ሕዝብ መብትና የኑሮ መሻሻል ተባብሮ መሥራት ነው፡፡ ማመን ያለበት የፖለቲካ ብልሃት፤ ሕዝብ ካመረረ በጋራ ከተነሳ ማንም ኃይል የማቆመው መሆኑን ነው፡፡ ውጣ ውረዱና የሚከፈለው መስዋዕት ከፍተኛ ቢሆንም በሕዝብ እምነት ያለው ቡድን ያሸንፋል፡፡ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ከሚያወግዘው ከደርግ አግዛዝ የተማረው አንድም ነገር የሌለ መሆኑን ማስተጋባት አግባብ አለው፡፡ ካለፉት ከወደቁ አምባገነኖች ሊማር ቢችልኖሮ ሕዝብ የጠላው አገዛዝ ንጹሕ ዜጎችን ቢገድል፤ ቢያስር፤ ቢደበድብ፤ ቢያቆስል እና ቢያሳድድ የተባበረን የሕዝብ አመጽ ሊቋቋም አይችልም የሚለውን ሁኔታ አይረሳውም ነበር፡፡ የደርግ አምባገነን አገዛዝ በአፍሪካ ተወዳዳሪ የሌለው የጦር ኃይል ነበረው፡፡ የግብጹ ሞባረክ በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ተወዳዳሪ የሌለው የስለላ መረብ፤ የጦርና የፖሊስ ኃይል፤ ግዙፍ ሀብት ነበረው ወዘተ፡፡ እነዚህ አምባገነኖች በተባበረ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ተንኮታኩተዋል፡፡

በጎንደር ሕዝብ ላይ የተካሄደውና አሁንም የሚካሄደው የግድያ፤ የእፈና፤ የማሳደድ ግፍ፤ በወጣት የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ የሚካሄደው ግድያ፤ እፈና፤ ማሳደድ ወዘተ. የሚያሳየን ተመሳሳይ ሁኔታ አለ፡፡ ይኼውም የሕወሓት አባቶችና ተተኪዎች ከቡድናቸው ጥቅምና ደህንነት ውጭ ለሌላው ኢትዮጵያዊ ሕይወት፤ ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ለሰብአዊ ክብርና ኑሮ ደንታ እንደሌላቸው በተከታታይ ዓይተናል፡፡ በቅርቡ በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር የድንበሩን ጉዳይ አስመልክቶ የተናገረው አግባብ አለው፡፡ «የድንበሩ ችግር አሁን የተነሳ ሳይሆን የቆየ ነው፤ አስቸጋሪ የሆነብን ከሥልጣኑ የተወገደውን ጎሳ የሚወክለው የአማራው ክልል ነው፤ አገሪቱን የሚገዛው በቁርቋም ማሕጸን የተወለደው የትግራይ ጎሳን የሚወክለው ሕወሓት ነው» ብሏል፡፡ የተቃዋሚው ክፍል ራሱንና ገዢውን ፓርቲ መጠየቅ ያለበት፤ አምባሳደሩ ይኼን ሲል ሁለት መንግሥታት አሉ ማለቱ ነው? ኢትዮጵያ በጎሳ ስለተከፋፈለች ዕድሉን ሕወሓት ስለሰጠን ተከታታይ መንግሥታት ያልተቀበሉትን ድንበር ለእኛ ይሰጥ ማለቱ ነው? አምባሳደሩ ጉዳዩ እስቸኳይ አይደለም ብሎ እየተናገረ ሕወሓት የግዋንን መስመር ሕጋዊ ለማድረግ ምን አስቸኮለው? ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኃይለማሪያም አንድም ሜትር መሬት የማይሰጥ ከሆነ ለምን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል አይገባም? ኢትዮጵያና ሱዳን የሚፈራረሙት የድንበት ውል ምን እንደሆነ ለምን ለሕዝብ ይፋ አያደርግም? በድንበሩ ዙሪያ የተቃዋሚው ክፍል አሁንም የተሳሳተ መረጃ ይከተላል፡፡ ለሱዳን የሚሰጠው ግዙፍ መሬት ኤርትራን ከሚያዋስነው የኢትዮጵያ ድንበር ጀምሮ እስከ ደቡብ ሱዳን እርዝመቱ 1,600 ኪ.ሜትር፤ ስፋቱ ከ20-60 ኪ.ሜትር የሚደርስ፤ ጎንደርን፤ ጎጃምን፤ ወለጋን፤ ከፋን፤ ጋሙ ጎፋንና ጋምቤላን የሚመለከት ለም መሬት ነው፡፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን ይመለከታል፡፡ ለኢትዮጵያ የወደፊት ደህንነት ጠንቅ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ ወዝቿን እንዳትጠቀም መሰናክል ይፈጥራል፡፡ ይኼም ራሱ የወቅቱ አንገብጋቢ የሆነ የጋራ ችግር ነው፡፡

በጎንደርም ሆነ በኦሮሚያ ገዢው ፓርቲ የክልሉን ደጋፊዎች፤ ፖሊሶችና ሌሎች እየተጠቀመ ዛሬ አንዱን ጎሳ፤ ነገ ሌላውን፤ ዛሬ አንዱን ሃይማኖት፤ ነገ ሌላውን ሲገድልና ሲያሳድድ ቆይቷል፡፡ ሆኖም፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ድምጽ ለማሰማት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ጩኸት በተናጠል፤ ለቅሶ በተናጠል፤ ትግል በተናጠል የት እንደሚያደርስን አላውቅም፡፡ ሕወሓት ይኼን ተከታታይ የመከፋፈል ባሕርይ ለመብቱ የሚነሳውን ሁሉ ለመቅጣት መሣሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ የሱዳኑ አምባሳደር የተናገረውን ስመረምር የሚናገረው የሕወሓትን ቋንቋ ነው፡፡ ከከፋፍለህ ግዛውን ቋንቋ አሁንም እየተጠቀመበት ነው፡፡ ቢጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ በጎንደር፣ በኦሮሚያና በሌሎች አካባቢዎች ፊት ለፊት ሆነው ወገኖቻቸውን የሚገድሉ፤ የሚያስሩ፤ የሚያደፍጡ የአካባቢው ደሞዝተኞች ናቸው፡፡ ችግሩ ከእነሱ አቅም በላይ ሲሆን የፌደራሉ ኃይል ይላካል፡፡ የሕወሓት አባላት በሳዊያን የሕወሓትን መርሀ የተቀበሉ አዲስ ተጠቃሚዎችና አዲስ ሕወሓቶች አሉ ማለት ነው፡፡ የበላይ አዛዡና ተቆጣጣሪው ሕወሓት እንዳለ ሆኖ፤ የኢሕአዴግ አባላት ቁጥር ከስድስት እስከ ሰባት ሚሊየን ይገመታል ሲባል ሁሉንም የጎሳ ፓርቲዎች ለመሰብሰብ ሞክሯል ማለት ነው፡፡ ዋናዎቹ የእድገት ተጠቃሚዎች የሕወሓት አባላት፤ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ይኼን ማለት ግን ሌሎች የፓርቲና የመንግሥት ኪራይ ሰብሳቢዎችና ሙሰኞች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ጎንደርም አሉ፤ ኦሮሚያም አሉ፤ ጋምቤላም አሉ ወዘተ፡፡ ሕወሓት ሲገዛ የቻለውና የሚችለው ሌሎችን በማባበልና በጥቅም በመደለል፤ የስልጣን አጋር ናችሁ በማለት፤ እኔ ከሌለሁ «ጠላቶቻችሁ የቂም በቀል ዘመቻ ያካሂዱባችኋል ወዘተ.» በማለት ነው፡፡ ኦሮሞውን አማራው ተመልሶ ሥልጣን ይዞ ይጨፈጭፍሃል፤ አማራውን ወዮልህ፤ ኦሮሞው ሥልጣን ከያዘ ያባርሃል፤ በጅምላ ይጨፈጭፍሃል፤ ትግሬዋን አማራውም፤ ኦሮሞውም አይምሮህም» እያለ ሕዝብ በፍርሃት ዓለም እንዲኖር አድርጎታል፡፡ ይኼ ሁኔታ በጋራ ጥቅም ምክንያት የጋራ አፈና እንዲካሄድ ረድቷል፡፡ ከላይ እንዳሳየሁት፤ የፖለቲካው አመራር በዚህ መልክ ከቀጠለ እድገቱም ቢኖር የእድገቱ ውጤት የሚጠቀመው ጥቂቶቹ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ገዢው ፓርቲ ከሥራ የሚወጡትን ባልደረቦቹንና በጡሮታ የሚወጡትን ተንከባክቦ ይይዛል፡፡

በጡሮታና በሌላ ምክንያቶች የሚወጡ ግለሰቦች ራሱ መንግሥት የሚሰጣቸው የጡሮታ አበልና ድጎማ ወይንም ፓርቲው በሚቆጣጠራቸው ድርጅቶች የሚሰጣቸው ሥራ ለምሳሌ የቦርድ አባልነትና ሊቀመንበርነት ተደማምረው የሚያሳዩት የገቢና የሀብት ክምችቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን ነው፡፡ በአሜሪካ የመካከለኛው መደብ ሠርቶ የሚያገኘው ወደ ታች እየወረደ ሲሄድ የአንድ በመቶው ክፍል ተብሎ የሚታወቀው መደብ የበለጠ ሀብት አከማችቷል፡፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው የገቢና የኃብት ስርጭት ሁኔታ በኢትዮጵያ በባሰ ደረጃ ይከሰታል የሚል እምነት አለኝ፡፡ አበበ ኃይለ ባቀረበው መረጃ መሠረት እያንዳንዱ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሚኒስትር ጡሮታ ሲወጣ ወይም ስትወጣ መንግሥት «በመቶ ሚሊዮን ብር ወጭ ተደርጎ ከፍተኛ ቪላዎች ከነመኖኛ ገንዳው ሊገነባላቸው ከወሰነ» እውነትም አገዛዙ በጥቅም ላይ የተመሠረተ እንጂ የድሃውን ሕዝብ ገቢና ሕይወት ለማሻሻል፤ የአገሪቱን እድገት ለማጠናከር፤ የመካከለኛ መደብ መሠረት እንዲጸኑ ለማድረግ አይደለም ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አያስቸግርም፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነቀርሳ ነው የሚል እምነቴ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም፤ በድሃው ሕዝብ ላይ የሚካሄድ ንግድ መቆም አለበት፡፡ አበበ ኃይለ «ይህች ሕዝብ በጉጉት የተከታተላት የመልካም አስተዳደር ችግር የመፍታት ውይይት ወደ ተግባር ተቀይራ የሕዝቡን እንባ የምታብስበት ዕለት በጉጉት እየተከታተለች መሆኑን መንግሥት አውቆ ተግባራዊ እርምጃ እንዲጀምር የበኩሌን ምክር እሰጣለሁ» ያለው ምክርና ምኞት ስኬታማ የሚሆን አይመስለኝም፡፡

ለማጠቃለል፤ ኢትዮጵያ የምትከተለው አድሏዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መርህ (Crony Capitalism) የጥቂቶች አገልጋይ መርህ ነው፡፡ «ፈጣን እድገት አለ ዳቦ የለም» የሚለውን ብሂል ስለሚያንጸባርቅ፤ ተከታታይና ፍትሐዊ እድገት ትርጉሙ-ቢስ ሆኗል፡፡ ችግሩ በማባበል፤ በዲስኩር፤ በግምገማ ወዘተ. የሚፈታ አይደለም፡፡ ገዢው ፓርቲ ስለመልካም አስተዳደር የፈለገውን ጥናት፤ ምርምርና ውይይት ቢያደርግ እመርታዊ የሆነ የሥርዓትና የመዋቅር ለውጥ አይቻልም፡፡ ተጠቃሚዎቹ አይፈቅዱም፡፡ የፖለቲካ ለውጥ ካልተደረገ የገንዘብና የኢኮኖሚ አመራር ለውጥ አይቻልም፡፡


ኮከብ ብርሃን
የባህል ሕክምና ማዕከል

ማንኛውም ባለጉዳይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በትህትና በማስተናገድ ላይ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ትክክለኛ ፈውስ የተገኘላቸው በሽታዎች በከፊል፡-

- ለሆድ ሕመም
- ለእጅና ለእግር ቁርጥማት
- ለአስም
- ለሾተላይ
- ለራስ ሕመም
- ለእግር ፈንገስ
- ለሚጥል በሽታ
- ለማዲያት
- እጅን ለሚጠባ
- ለትምህርት
- ለእጅ ሰብእ
- ለጭርት ወይም ማሳከክ
- ለአይነ ጥላ
- ለወር አበባ መብዛት
- ሌሊት ለሚሸና

በተለይ የብዙ ሰዎችን ችግር የሆነውን የስንፈተ ወሲብ /በመቀባት/ ብቻ ፈውስ ይሰጣል፡፡

አድራሻ፡-
ሐና ማርያም ቀለበት መንገድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት
ለበለጠ መረጃ፡- 0911 808241 /0913 778746/ 0912 635069
በእውነት ስለ እውነት እንነጋገር!!



# ታሪክና ኅብረተሰብ

ታዴዎስ ታንቱ
(የስልክ ቁጥር:- 0934996138 ፣ የመ.ሳ. ቁጥር:- 43414)

# “አብዮቱና ትዝታዬ” ሲፈተሽ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ፕሬዝዳንት የነበረው የቀድሞ የደርግ አባል ጓድ ፍስሐ ደስታ ሰሞኑን አንድ የታጠፈ ብርድ ልብስ የሚያክል መጽሐፍ ተብዬ ጥራዝ ለገበያ አቅርቦ ይቸበችባል። ጥራዙ ‹‹አብዮቱና ትዝታዬ›› በሚል ርእስ ሥር ተደራጅቷል። ጓድ ፍስሐ ደስታ ከመነሻው አንስቶ የዐቢይ ደርግ አባል እንደነበረ ይታወቃል። በጊዜው የኢትዮጵያን ሁኔታ የተከታተለ ሁሉ ጓድ ፍስሐ ከመነሻው አንስቶ የዐቢይ ደርግ አባል እንደነበረ ያስታውሳል። ጓድ ፍስሐ የትግራይ ተወላጅ ነው። በዚህ ምክንያት በጥራዙ ውስጥ ሌ/ጄኔራል አማን ከተባለ ከሀዲ አንስቶ ለትግሬዎች (የባሕር ምድር ተወላጆችን ጨምሮ) ሲቆረቆር ይስተዋላል። ‹‹ዘር ከልጓም ይስባል›› ይባል የለ?

ጓድ ፍስሐ ደስታ በጥራዙ ፊት ለፊት ሽፋኑ ላይ የሌ/ኮሎኔል ማዕረግ አድርጎ ከጓድ አዲስ ተድላ ጎን ቆሞ ይታያል። ይህንን ለማድረግ ለምን እንደፈለገ አይገባንም። ግለሰቡ ለደርግ አባልነት ሲመረጥ ሌ/ኮሎኔል እንዳልነበረ ይታወቃል። እርግጥ ነው በሒደት ማዕረጉን አጥልቋል። ነገር ግን ቆየት ብሎ በወታደራዊ ማዕረግ ከመቀጠልና ‹‹ጓድ›› እየተባለ በሲቪል ደረጃ ከመታገል የትኛው እንደሚሻለው ተጠይቆ ወታደራዊ ማዕረጉን በራሱ ፈቃድ አሽቀንጥሮ በመወርወር የኋለኛውን የትግል አጋርነት ማዕረግ በቅጽ አረጋግጦ ወንበዴ ወገኖቹ የኢትዮጵያን ሥነ መንግሥት እርካብ እስከረገጡበት ጊዜ ድረስ በጓድነት ቆይቷል። አሁን ታዲያ የሌ/ኮሎኔል ማዕረግ በፊት ለፊት ሽፋኑ ላይ የለጠፈው ቆጭቶት ይሆን እንዴ? ቅሌት በየት በኩል ይመጣል? እስቲ ንገሩኝ ወገኖቼ?

በመሠረቱ ማንኛውም ትግሬ በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛ ለንባብ የሚያቀርበው ሕትመት ለሒስ ይመቸኛል። ምክንያቱም በአንደኛ ደረጃ የሞተ አማርኛቸውና እንግሊዝኛቸውም ያዝናናኛል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የእነርሱ ሐሳብ ከሰው ሐሳብ ጋር ስለማይገጥም ሐሳባቸውን እየመዘዝኩ እፈላሰፍባቸዋለሁ። ጓድ ፍስሐ ደስታም መረጃ ሳይሆን 598 ገጾች ያሉት መዝናኛ ስላቀረበልኝ ከልብ አመሰግናለሁ። እናንተም ተዝናኑ። የትናንት ፍስሐን በዛሬው ፍስሐ ውስጥ ፈልጉት። የለም እኮ! ሔደ! ነጎደ!

የቀድሞ የኢሕዴሪ ምክትል ፕሬዝዳንት ጓድ ፍስሐ ደስታ በዘመኑ ከሠራዊቱ ለደርግ አባልት ተመርጠው ከተላኩት በሕይወት የተረፈ ብቸኛው የባህር ምድር (ትግሬዎችንም ጨምሮ) ትግርኛ ተናጋሪ ነው። የተቀሩት ትግሬ የደርግ አባላት በሙሉ በቅብብሎሽ በወረሱት የቅሌት ሕመም ሳቢያ በአብዮቱ ሒደት ቃለ መሐላቸውን አፍርሰው እንደ ስሙኒ ጌሾ ቀልለው በመገኘታቸው በጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና በተቀሩት እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ውሳኔ ተደምስሰዋል። ከአፈር ጋር ተዋሕደው ወደ ታሪክ ትቢያነት ተለውጠዋል። ስማቸውን መጥቀስ ይቻላል። 1) ሌ/ጄኔራል አማን አንዶም (የደርግ ሊቀመንበር)፣ 2) ኮሎኔል ኀሩይ ኃይለ ሥላሴ፣ 3) ሻምበል ሞገስ ወ/ሚካኤል፣ 4) ሻምበል በላይ ጸጋዬ፣ 5) መ/አለቃ ተስፋዬ ተክሌና 6) ጁኔር ኢክማን ዮሐንስ ፍትዊ ናቸው። ቆየት ብሎ ደግሞ ሻለቃ ኪሮስ ዓለማየሁ ተገድሏል። እርግጥ ነው በወቅቱ ኪሮስ ዓለማየሁ ራሱን በገንዛ እጁ እንዳጠፋ ተነግሯል። ይህን ግን ማመን ይከብደናል። እስር ቤት ውስጥ ሆኖ የገዛ ሕይወቱን በገዛ እጁ እንዴት ሊያጠፋ ይችላል? የመርዝ እንክብል ይዞ ገብቷል እንዴ? በፍጹም ሊታመን አይችልም። ከጭቁኑ መለዮ ለባሽ አፈንግጦ በአቋም ቅሌት ምድር ውስጥ ካሉት ዘመዶቹ ጋር ተቀላቅሏል።

ያም ሆነ ይህ ጓድ ፍስሐ ደስታ በሕይወት ሊቆይ የቻለው ከተደመሰሱት ትግሬ የደርግ አባላት የተለየ አቋም ኖሮት አልነበረም። በአብዮቱ ሒደት የኃይል ሚዛኑን በእርጋታ እያስተዋለ አቋሙን ደብቆ በአድርባይነት ነፍሱን ጠብቆ የኖረ ለራሱ የሚያውቅበት ብልጥ ሰው ስለሆነ እንደነበር ልናውቅ ይገባል። ይህ ሰው ሞኝ እየመሰለ የተካነው ብልጠቱ ዛሬ ወገኖቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት አዛዥና ናዛዥ ለሆኑበት የጨለማ ዘመን አድርሶታል። አድርባይነት በወዝ አደሩ ርዕዮተ ዓለም ታላቅ የሥነ መንግሥት ወንጀል መሆኑ በአስተምህሮው ተመልክቷል። ጓድ ፍስሐ ደስታ ግን ብልጠት ሲታከልበት አድርባይነት ሳይነቃበት የኖረ ግለሰብ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል።

የኢሕዴሪ ምክትል ፕሬዝዳንት ጓድ ፍስሐ ደስታ ለገበያ ባቀረበው ጥራዙ በአቀራረቡ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. የዘውድ ሥርዓት አገዛዝ ባለሥልጣናትን ለመደምሰስ በታላቁ ቤተ መንግሥት በተካሔደው ስብሰባ ላይ አስተያየት የሰጡ የደርግ አባላትን በተዘዋዋሪ መንገድ ይኮንናቸዋል። ራሱን ነጻ ለማድረግም ይዳዳዋል። አብሮ አቡክቶ ጋግሮና በልቶ ጤንነት ሲሰማው ከኖረ በኋላ አሁን ዙፋን ላይ ከተቀመጡ ወገኖቹ ክብርና ሞገስ ለማግኘት በአቋም ለውጥ ሲያፈነግጥ ይስተዋላል። ዘር ከልጓም ይስባልና። ቀንጭበናል ‹‹ከዚያ በኋላ›› ይላል ጓድ ፍስሐ ደስታ። ‹‹ከዚያ በኋላ አንዳንድ ተሰብሳቢዎች እየተነሱ ሳይቀድሙን መቅደም አለብን በማለት በስሜታዊነት ይናገሩ ጀመር። ሁኔታው እየተጋጋለ ሲመጣ ሻለቃ መንግሥቱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ጉዳዩ ማምራቱን ሲገነዘቡ የሁላችሁም አስተሳሰብ ይህ ከሆነ የመርማሪ ኮሚሲዮን ድርቁን በመደበቅ ተጠያቂ ናቸው ባላቸውና በከፍተኛ ወንጀልና በአገሪቱ ውድቀት ተጠያቂ በሆኑት ላይ ውሳኔ ውሳኔ ወደመስጠት እናምራ አሉ›› (ገጽ 123) በማለት ያስነብበናል።

ጓድ ፍስሐ ደስታ ‹‹… በስሜታዊነት…›› ሲል

> ጀኔራል አማን ቤቱ በታንክ ተደርምሶ ሰዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ ነፍሱ ገና እንዳልወጣች በአንድ ወቅት በሕትመት ላይ ቀርቦ ተነቧል። ወደ ውስጥ ከገቡት ሰዎች መካከል አንድ የደህንነት አባል ግንባሩን በሽጉጥ ብሎ እንደጨረሰው ተነግሯል

ምን ለማለት ፈልጎ ነው? አንዳንድ የደርግ አባላት በስሜታዊነት ሲናገሩ እሱ ከእነሱ በዕውቀት፣ በአስተዋይነትና በምክንያታዊነት የላቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሐሳብ በወቅቱ ለስብሰባው አቅርቦ ከሆነ አሁን ቃል በቃል ለምን አልነገረንም? ጅብ ከሄደ ውሻ ለምን ይጮኻል? በወቅቱ የደርግ አባላት በእያንዳንዱ ባለሥልጣን ላይ እጃቸውን ሲሰቅሉ ከአሸናፊው ድምጽ ጋር ወግኖ ሕይወቱን ጠብቆ ያዳነ ግለሰብ አሁን የደርግ አባላትን በስሜታዊነት ለመክሰስ ከቶም የሞራል ብቃት የለውም። በስብሰባው ያልተሳተፈ ከሆነ ደግሞ አንዳንድ የደርግ አባላት ስሜታዊነትን እንዳንጸባረቁ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ጓድ ፍስሐ ደስታን የሚያንገበግበው ትግሬ ሹማምንት ከተቀሩት የዘውድ ሥርዓት አገዛዝ ባለሥልጣናት ጋር አንድ ላይ መረሸናቸው መሆኑ ይገባናል። ዙሪያ ጥምጥም ለምን ይኬዳል? እኛን የሚያንገበግበን ግን ከነአባቱ ባንዳ ራስ መንገሻ ስዩም አምልጦ በመሄድ ዛሬም በሕይወት መኖሩ ነው። ይህ ዕድሜውንና የመደብ ጀርባውን ማመዛዘን እንኳን የተሳነው ግለሰብ ‹‹ብኛ የተጀመረው በልጆቻችን ተፈጽሞ አየነው›› በማለት በደረሰበት ሁሉ አሁን በሥልጣን ላይ የተኮፈሰውን ቡድን ሲያሞግስ ይስተዋላል። ትንሽ መቼም፣ ምንግዜም ትንሽ ነውና።

ያም ሆነ ይህ በደምጽ ብልጫ በተወሰነ ጉዳይ አንዱ ስሜታዊ የተቀረው ምክንያታዊ ተብሎ ሊለይ የሚችልበት ሁኔታ አይታየንም። እያንዳንዱ ሰው ያመነበትን ሐሳብ የመሰንዘር መብት ነበረውና። አንድ ሰው ከማንም ሐሳብ ሳይመገብ በስሜቱ ብቻ ተነድቶ አቋም በመውሰድ የፈጸመው ጉዳይ ቢሆን ኖሮ የጓድ ፍስሐ ደስታን ሐሳብ ለመጋራት አናቅማማም ነበር። ጓድ ፍስሐ ደስታ ከመነሻው አንስቶ በተወሰነበት ጉዳይ አንዳንድ የደርግ አባላትን በስሜታዊነት ሲከስ ስንሰማ እናዝንለታለን እንጂ ፈጽሞ አናዝንበትም።

በመቀጠል ጓድ ፍስሐ ደስታ ‹‹…. ወደሚፈልጉት አቅጣጫ…›› ብሏል። የጥራዙ ጸሐፊ ጓድ መንግሥቱን ለመወንጀል ሲል በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ አውቆ ለመጠምዘዝ ይሞክራል። እውነታው ግን ይለያል። አሸናፊ ሆኖ የወጣው የጓድ መንግሥቱ ብቻኛ ሐሳብ አልነበረም። ይልቁንም የተቀሩት የደርግ አባላት ሐሳብ እንደነበር ልናውቅ ይገባል። ብዙ የደርግ አባላት የዘውድ ሥርዓት አገዛዝ ባለሥልጣናት ከተያዙበት ወቅት አንስቶ እንዲገደሉ ሐሳብ ያቀርቡ እንደነበር ጓድ ፍስሐ አሳምሮ ያውቃል። በተለይም ንዑስ ደርጎች ባለሥልጣናቱ ካልተገደሉ ሥራ እስከማቆም ያሻቀበ እርምጃ እንደሚወስዱ ተናግረዋል። አንዳንድ የጦር ክፍሎችም ባለሥልጣናቱ በአስቸኳይ እንዲገደሉ ሐሳብ አቅርበዋል። ለማስረጃም የጎፋ ሰፈር ጦር አጥብቆ እንደጠየቀ መጥቀስ ይቻላል። ጓድ ፍስሐ በወቅቱ ይህን አልሰማም ለማለት አንችልም። ታዲያ የግድያ ሐሳብ በጓድ መንግሥቱ ብቻ ተረግዞ የተወለደ ለማስመሰል ለምን ይሞከራል? እርግጥ ነው ጓድ መንግሥቱ ባለሥልጣናቱ እንዲገደሉ ፈልጓል። ነገር ግን ከእርሱ አካሄድ በፈጠነ ሁኔታ ባለሥልጣናቱ ባስቸኳይ እንዲገደሉ ሠራዊት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡም ሐሳብ ያቀርብ እንደነበር ሊታወቅ ይገባል። እኔም አንዱ ነኝ ምን ታወራለህ?

ጓድ ፍስሐ ደስታ በድልቡ ጥራዝ ውስጥ ጄኔራል አማንን ከልክ በላይ ሲያሞግሰው ይስተዋላል። ወደ ሰማያተ ሰማይም ያደርሰዋል። እንደ ጣዖት ሊያመልከውም ይዳደዋል። እንደገና ሥልጣን ቢያገኝ በስሙ ጽላት ሳይቀርጽ አይቀርም። እንከን የለሽ ያደርገዋል። ትግሬ በመሆኑ ብቻ ያወድሰዋል። አንድ ጄኔራል እንደ ሕፃን ልጅ አኩርፎ እንዴት ሳምንት ሙሉ እቤቱ ይጋደማል? ጓድ ፍስሐ ይህንን እንጭጭ ጄኔራል ሲያሞግስ ለሕሊናው እንዴት እንዳልከበደው አልገባኝም። ደግሞስ በየትኛው ጀግንነትን በሚፈትን በተራዘመ ጦርነት ተፈትኖ ያውቃል? ሶማሌ ነጻ እንደወጣች ጥቂት ተታኩሷል። አታኩሷልም። ታዲያ ከሶማሌ ጋር መዋጋት የጀግንነት አልፋና ኦሞጋ ነው እንዴ? ጓድ ፍስሐ ደስታ አማንን ለማሞገስ አማርኛውን ሁሉ አሟጦ ጨርሷል። ድሮም የአማርኛ ችግር ነበረበት። ምን ይደረግ? አሁንም ዘር ከልጓም ይስባል እንበላ! በጥቂቱ ቀንጭበናል ‹‹መጨረሻም አንድ ታንክ ቤቱን ደርምሶ ሲገባ ጄኔራሉ ዩኒፎርማቸውን እንደለበሱ ሽጉጣቸውንና ዐዚያቸውን አጠገባቸው አድርገው ራሳቸውን ገድለው ተገኙ›› (ገጽ 124) በማለት ይነግረናል ጓድ ፍስሐ ደስታ።

የኢሕዴሪ ም/ፕሬዝዳንት ጓድ ፍስሐ አንዳንድ ሁነቶችን በግምት ይናገራል። ምናልባትም የአማንን ዝና ከፍ ለማድረግ ሲል አውቆ መዋሸቱ ሊሆንም ይችላል። አይታወቅም። እውን ጄኔራል አማን ሕይወቱን በገንዛ እጁ አጥፍቷ? ፈጽሞ ሐሰት ነው። ጄኔራል አማን ሕይወቱን በገንዛ እጁ አላጠፋም። በድህረ ወያኔ በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች ጄኔራል አማንን በማስመልከት ጽፈዋል። ነገር ግን አንዳቸውም ሰውየው ራሱን ለመግደሉ የከተቡት ነገር አልነበረም። ጓድ ፍስሐ ደስታ ራሱን ለመግደሉ ሲናገር የመጀመሪያው ሰው ነው። ራሱን የሚገድል ከሆነ እንደአይጥ በሌማትና በአከንባሎ ሥር እየተሹለከለከ ለምን ለአንድ ሳምንት ያክል ጊዜ ሰነበተ? ወዲያው ጠጥቶ ለምን አልተገላገለም? ዳዊት ሲደግም ወይስ ጠጠር ሲቆጥር ሰነበተ? ያም ሆነ ይህ ስለ ጄኔራል አማን በመጽሐፍ ከተጻፈው ለክርክራችን ማጎልበቻ እንደወረደ ቦጭቀናል። እንዲህ ይነበባል:-

‹‹መስማማት ከከሸፈ ከሦስት ቀናት በኋላ ቡድኑ ምናልባት በጉዳዩ ሦስተኛ ክፍለ ጦርን ጄኔራሉ ያስተባብር ይሆናል በሚል ሥጋት በቀቢጸ ተስፋ ሥልጣናቸውን ለመከላከል ጠንካራ እቅድ አወጣ። ከማታው በአንድ ሰዓት ላይ ከሁለት ወራት በፊት ርእሰ ብሔርና ርእሰ መንግሥት በማለት ወደ ሾሙት ሰው ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ላኩ። ጄኔራል አማን በተኩስ በተኩስ ልውውጥ ተገደለ። በእለቱ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት ከየእስር ቤቱ ተለቅመው ወደ ዋናው ወሕኒ ቤት ግቢ ተወስደው ተረሽነዋል።

Three days after the disagreement with the general, the group thought he might call in the Third Division to deal with them. So they embarked on a desperate and drastic plan to protect their position. They sent an armored car at 7:00 PM to the home of the man whom they had declared head of state and government just two months before. General Aman was killed killed in an exchange of fire. This was the day officials of the former government were collected from their various places of detention and taken to compound of the main prison where they were machine-gunned.›› The Emperor's Cloth's, P# 189.

ጄኔራል አማን ራሱን በራሱ እንዳልገደለ እዚህ ላይ በግልጽ ተመልክተናል። ጓድ ፍስሐ የደርግ አባል ሆኖ ይህን ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም። አሳምሮ ያውቃል። ነገር ግን ለአማን የታሪክ ትርፍ ለማስመዝገብ ፈልጎ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ጀኔራል አማን ቤቱ በታንክ ተደርምሶ ሰዎች ወደ ውስጥ ሲገቡ ነፍሱ ገና እንዳልወጣች በአንድ ወቅት በሕትመት ላይ ቀርቦ ተነቧል። ወደ ውስጥ ከገቡት ሰዎች መካከል አንድ የደህንነት አባል ግንባሩን በሽጉጥ ብሎ እንደጨረሰው ተነግሯል። ይህ ደግሞ እውነት ይመስላል። ምክንያቱም በማግስቱ እሁድ ዕለት የወህኒ ቤት ተረኛ የነበሩና ጄኔራል አማንን በሚገባ የሚያውቁ ፖሊሶች ሬሳው ግንባሩ ላይ የተበሳ መሆኑን ዛሬም ይናገራሉና። ደግሞ የባንዳ ልጅ መቼ ራሱን ገድሎ ያውቃል? ጀኔራል አማን ከባሕር ምድርና ከትግራይ ባንዳዎች የተወለደ ግለሰብ ነው። አማን እንደተገደለ ብዙ ሰዎች ወሬ ሰምተው ሲቀባበሉ ተስተውለዋል። አንዳንዶች ለባለሥልጣናት እልቂት አማን ምክንያት እንደነበር ሲናገሩ ተሰምተዋል። የተቀሩት ደግሞ ‹‹ድሮም እነርሱ ቅሌታሞች አይደሉም እንዴ?›› ሲሉ ተደምጠዋል።

ጓድ ፍስሐ ደስታ በጥራዙ የዘውድ ሥርዓት አገዛዝ ባለሥልጣናቱ አገዳደል ሒደቱንም የማያውቅ ለመምሰል ሲሞክር ይስተዋላል። ከቅጥፈት ምን እንደገበየ እሱ ራሱ ብቻ ያውቃል። ከጥራዙ ቀንጭበናል።

ከምሽቱ በሁለት ሰዓት ከወደ ወህኒ ቤት ከባድ ተኩስ ተሰማ። ለምን እንደሆነ ሳይታወቅ ከድንጋጤ የተነሳ በግቢውም ውስጥ የመትረየስ ተኩስ ጀምሮ ወዲያው ተቋረጠው አስቆሙት። ከወደ ወህኒ ቤት የተሰማው ተኩስ የሞት ውሳኔ የተላለፈባቸው ሐምሳ ዘጠኝ ባለሥልጣናት ሲገደሉ ነበር። የጄኔራል አማንና የእነዚህ ባለሥልጣናት ቀብርም በዚሁ በወህኒ ቤት ተፈጸመ። (ገጽ 124)።

የኢሕዴሪ ም/ፕሬዝዳንት ጓድ ፍስሐ ደስታ ‹‹… ባለሥልጣናት…›› ማለት ምን ማለት እንደሆነም የሚያውቅ አይመስለንም። ራሱ ባለሥልጣን ሆኖ የባለሥልጣንን ትርጉም ሲያጣ ያሳፍራል። በዚያን ዕለት ዐሥር አለቃም ተገድሏል። ተራ ወታደርም ተገድሏል። እነዚህ ባለሥልጣናት ነበሩ እንዴ?

የጥራዙ ጸሐፊ በደርግ ውሳኔ ስለተገደሉት ባለሥልጣናት፣ ጄኔራል መኮንኖች፣ ከፍተኛ መኮንኖችና የበላይ ሹማምንት የሞት ቅጣት በተኩሱ ሳቢያ የሰማ ለመምሰል ይሞክራል። ማን ያምነዋል? ‹‹… በግቢውም ውስጥ የመትረየስ ተኩስ ጀምሮ…›› ይላል። ይህ አሁን ይታመናል? በፍጹም ውሸት ነው። አንድ ወታደር ሌላ ሰው ስለተኮሰ ከመሬት ተነስቶ ዝም ብሎ አይተኩስም። ጓድ ፍስሐ ጥራዙ የታተመው ለሕፃናት ነው እንዴ? ወህኒ ቤት ቅጥር ግቢ ተኩስ ስለተሰማ በቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ መትረየስ ፈጽሞ አይተኮስም። መትረየስ አስተኳሹ ማን ነው? ምን ዓይቶ አስተኮሰ? አንድ ወታደር የአጸፋ ተኩስ ከማሰማቱ በፊት ጠላት የት ቦታ እንዳለ ማወቅ አለበት። ለምን ዓላማ ተኮሰ? ምን ዓይነት መሣሪያ ተኮሰ? የት ቦታ ሆኖ ተኮሰ? አጸፋ ባይሰጥስ ምን ይከተላል? እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ያነሳል። ያለ ትእዛዝ ደግሞ አይተኮስም። ወታደራዊ ዲሲፒሊን በታላቁ ቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ውስጥ የለም እንዴ?

ይቀጥላል…

# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

## በሁሉም መጻሕፍት መደብሮች ያገኙታል




# አዲስ የግጥም መድበል በገበያ ላይ!

## መጽሐፉን በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ባሉ የመጻሕፍት መደብሮች ያገኙታል።




የሀገር ፍቅር፣ ፖለቲካና እምነት ተሰናስለው የቀረቡበት በዓይነቱና በአቀራረቡ ልዩ የሆነ የግጥም መድበል ለገበያ ቀረበልዎ! መድበሉ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪ በሆነው መምህር ምንዋጋው ተመስገን ተዘጋጅቶ ለንባብ የበቃ ነው። "ዓለማዊ" እና "መንፈሳዊ" በሚል በሁለት ክፍሎች የተካተቱት 52 ግጥሞች እንደሀገር የገባንበትን ሞራለ ቢስነትና ሆድ አምላኩነት ፍንትው አድርገው የሚያሳዩን ናቸው።

# መንቶች የዕጽዋት (የባህል) መድኃኒት ማምረቻና መሸጫ

## MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER



ይህ የዕጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረውን የአባቶች የባህል (እጽዋት) መድኃኒት ሕክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባዕድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነው። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

### በሚወሰድ

- ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።
- ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።
- የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን።

የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆንም ኮሌስትሮል ያጠፋል።

- ለነርቭ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።
- ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።
- ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።
- ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይስስ ጭምር ያድናል።
- ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።
- በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።
- ‹‹ሽንት ለሚያስቸግረውና ለስኳ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አለን››

### የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት

- ለኪንታሮት (ፌስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባላዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።
- ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል
- ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታሮት በሽታ መድሀኒት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

ቁጥር 1፡ አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሐና ማርያም ከጤና ጣቢያው 100 ሜትር አለፍ ብሎ
ቁጥር 2፡ ሰሜን ሸዋ መሐል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊትና ወይን መድሐኒዓለም ፊት ለፊት
ቁጥር 3፡ መገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድሐኒት መሸጫና ነጻ የመረጃ ማዕከል
ቁጥር 4፡ ጎጃም በረንዳ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ካለበት ሕንጻ ላይ 2ኛ ፎቅ 221 ቁጥር የመድሐኒት መሸጫና ነጻ የመረጃ ማዕከል
0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886